# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ 81ኛ ዓመት ቁጥር 235 ሚያዝያ 25 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!












ፎቶ - ሃይሽ አብርሃ

# ኢትዮጵያ የፍቅር ሃገር ሆና እንድትቀጥል ሁሉም እንዲተባበር ጥሪ ቀረበ

## • 1443 ኛ የኢድ አልፈጥር በዓል ተከብሯል

ዘላለም ግዛው

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ሕዝቦቿ የሚፈቃቀሩባት፣ በሰላም ወጥተው የሚገቡባት፣ የፍቅር ሃገር ሆና እንድትቀጥል ሁሉም በሚያቀራርቡ ተግባራት ላይ ሊተባበር እንደሚገባ የአዲስ አበባ እስልምና ከፍተኛ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሼህ ሱልጣን አማን ጥሪ አቀረቡ፡፡

1443ኛ ዓመተ ሂጅራ የኢድ አልፈጥር በዓል ትናንት በአዲስ አበባ ከተማ ሲከበር ሼህ ሱልጣን አማን እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ በሰላም ወጥተው የሚገቡባት፣ የፍቅር አገር እንድትሆን ሁሉም በሚያቀራርቡ ተግባራት ላይ ሊያተኩር ይገባዋል፡፡

በኅብረተሰቡ ውስጥ መለያየት፣ መራራቅና ግጭትን የሚፈጥሩ ተግባራት ማድረግ እምነቱ አያዝም፡፡ አንድነት ለሃገርም ለወገንም የሚጠቅም በመሆኑ ዑለማዎች ውስጣቸውን ፈትሸው ለሰላምና ለአንድነት መቆም እንደሚገባቸው መክረዋል፡፡

ኢትዮጵያ የፍቅር... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






# በጠላቶች ሴራና በባንዳዎች ተባባሪነት ኢትዮጵያን የማተራመስ ውጥን እንደማይሳካ መንግሥት አስታወቀ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- በታሪካዊ የኢትዮጵያ ጠላቶች ሴራና በውስጣዊ ባንዳዎች ተባባሪነት ሃገርን የማተራመስ ውጥን እንደማይሳካ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት አስታወቀ።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ባወጣው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ በአዲስ አበባ የታላቁ ዒድ ሰላት ላይ በተፈጠረ ችግር በንብረት እና በፀጥታ ኃይሎች ላይ ከደረሰው መለስተኛ ጉዳት ውጭ በአብዛኞቹ የሃገሪቱ አካባቢዎች የ1443ኛው ኢድ አልፈጥር በዓል ሰላት በደማቅ ሁኔታ ተካሂዶ በሰላም ተጠናቋል።

የውስጥ ባንዳዎች በሃይማኖት ሽፋን ከውጭ ኃይሎችና ከታሪካዊ ጠላቶች ጋር ተቀናጅተው ማኅበራዊ

በኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት
FDRE Government Communication Service

በጠላቶች ሴራና... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# በሃይማኖት ሽፋን የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች በሕግ እንዲጠየቁ የእስልምና እምነት ተከታዮች ጠየቁ

ውብሸት ሰንደቁ

አዲስ አበባ፡- ሃይማኖትን ሽፋን በማድረግ ሕዝብን ከሕዝብ ለማጋጨትና ተሳስሮና ተከባብሮ በኖረ ማኅበረሰብ መካከል ጥርጣሬ ለመፍጠር የሚንቀሳቀሱ ኃይሎችን መንግሥት በሕግ ተጠያቂ ሊያደርጋቸው እንደሚገባ የእስልምና እምነት ተከታዮች ገለፁ፡፡



አራጌ አሊ



ሼህ መከተ ሙሄ



ኢብራሂም ከድር

ፎቶ - ሃይሽ አብርሃ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ያነጋገራቸው የእስልምና እምነት ተከታዮች እንደገለፁት፤ ሃይማኖትን ሽፋን በማድረግ ሕዝብን ከሕዝብ ለማጋጨትና ተሳስሮና ተከባብሮ በኖረ ማኅበረሰብ መካከል ጥርጣሬ ለመፍጠር የሚንቀሳቀሱ ኃይሎችን መንግሥት በሕግ ተጠያቂ ሊያደርጋቸው ይገባል፡፡

አስተያየታቸውን የተናገሩት አቶ አራጌ አሊ እንደተናገሩት፤ በአንዳንድ አካባቢዎች በሃይማኖት ሽፋን የሚፈፀሙ ተግባራት ኢትዮጵያን ለመሰለች የመቻቻል

በሃይማኖት ሽፋን... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







# "በህዳሴው ግድብና በፋይናንስ ተቋማት ላይ ያነጣጠሩ የሳይበር ጥቃቶች ከሽፈዋል"

## - የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- በህዳሴው ግድብና በከፍተኛ የፋይናንስ ተቋማት ላይ ያነጣጠሩ የሳይበር ጥቃቶች መክሸፋቸውን የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ገለፀ።

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ሹመቴ ግዛው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያን መልካም ነገር ማየት በማይፈልጉ የውስጥና የውጪ ኃይሎች የሚደገፉ አካላት ህዳሴው ግድብ ላይ በተቀናጀ መልኩ የሳይበር ጦርነት ከፍተው ነበር። ጥቃቶቹ ምንም ጉዳት ሳያደርሱ እንዲመክኑ ተደርጓል።

በተመሳሳይም በኢትዮጵያ ከፍተኛ የፋይናንስ ተቋማት ላይ ያነጣጠሩ በርካታ የሳይበር ጥቃቶች በባለሙያዎች ጥረት እንዲከሽፉ ተደርጓል ሲሉ ተናግረዋል።

የሃገሪቱን ሰላምና ዕድገት በማይፈልጉ ሃገራት የሚደገፍ ድርጅት የህዳሴው ግድብ ግንባታን ለማስተጓጎል በማቀድ 'ብላክ ፒራሚድ ወር' በሚል ስያሜ የሳይበር ጦርነት ከፍቷል። ይሁንና የጥፋት አላማ አቅደው ሲያሴሩ የነበሩት ሁሉ እንዳሰቡት ሕልማቸው ሳይሳካ ተጨናግፏል ብለዋል።

ዋና ዳይሬክተሩ እንዳስታወቁት፤ ከህዳሴው ግድብ ውኃ ሙሌት ጋር በተያያዘ ብላክ ፒራሚድ ወር የሚባል የኮምፒውተር ቫይረስ ተሠርቶ ጥቃት ለማድረስ ሙከራ ተደርጓል። በተለይም የፋይናንስ ተቋማት



ዶክተር ሹመቴ ግዛው

የሚጠቀሙባቸውና እርስ በእርሳቸው የተሳሰሩ 37 ሺህ ኮምፒውተሮችን ላይ ጥቃት በመፈጸም የህዳሴው ግድብን ለማስተጓጎል ተሞክሯል።

ጥቃቶቹም በኢንፎርሜሽን ደህንነት አስተዳደር ጥብቅ ክትትል ምንም ጉዳት ሳያስከትሉ እንዲቋረጡና እንዲመክኑ መደረጋቸውን አስታውቀዋል። ፡

የህዳሴው ግድብ ኃይል ማመንጨት ከጀመረ በኋላ የሚሰነዘሩ የሳይበር ጥቃቶች ተጠናክረው ሊቀጥሉ እንደሚችል ይገመታል ያሉት ዶክተር ሹመቴ፤ ከዚህ በኋላም የሳይበር ምሕዳሩን በመጠቀም ግድቡ በአግባቡ ኃይል እንዳያመነጭና እንዲቆም ጥረት ሊያደርጉ የሚችል አካላት እንደሚያደርጉ ይጠበቃል ብለዋል።

ለዚህም ጠንካራ የሳይበር ደህንነት ተግባራዊ በማድረግ ከህዳሴው ግድብ ግንባታና ቁጥጥር ተቋማት ጋር በቅርበት እየተሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ ግድቡን በተመለከተ ከአመራረት እስከ ግንባታ ዕቃዎች ማጓጓዣ የሚያጠቃልሉ ሥራዎች ላይ የሳይበር ምህዳሩን በመጠቀም ከፍተኛ ክትትል ይደረጋል ብለዋል።

በህዳሴው ግድብ ላይ የሚቃጡ የሳይበር ጥቃቶች እስካሁን ምንም ዓይነት ጉዳት ሳያደርሱ እንዲመክኑ ቢደረግም አሁንም የፋይናንስ ተቋማት ላይ ተመሳሳይ ጥቃቶች እየተሰነዘሩ መሆኑን አስታውቀዋል።

እንደ ኢነርጂ ተቋማት ሁሉ ፋይናንስ ተቋማትም በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሚደረጉ የሳይበር ጥቃቶች ዒላማ መሆናቸውን ጠቁመው፤ የሳይበር ጥቃቶችን ለመከላከል ሁልጊዜም አንድ እርምጃ ቀድሞ ማየት፣ ማቀድና መተግበር ያስፈልጋል ብለዋል።

በፋይናንስ ተቋማት ላይ የሚሰነዘሩ የሳይበር ጥቃቶች ሰብረው መግባት ከቻሉ መዘዛቸው ብዙ እንደሆነ የጠቆሙት ዋና ዳይሬክተሩ፤ የተቃጡት ጥቃቶች ቢሳኩ ኖሮ በፋይናንስ ተቋማት ላይ ብቻ ሳይሆን በሃገር ደረጃ ከፍተኛ ችግር ያስከትሉ እንደነበር ገልጸዋል።

የፋይናንስ ተቋማትን ከጥቃት ለመከላከል ልዩ ትኩረት እናደርጋለን ያሉት ዶክተር ሹመቴ፤ ይሁንና ተቋማቱም ከነዚህ ዓይነት ጥቃቶች ራሳቸውን ለመጠበቅና ለመከላከል አስፈላጊ የሚባሉ ዝግጅቶችን ማድረግ አለባቸው ሲሉ አሳስበዋል።

በተለይ የፋይናንስ ተቋማት የሳይበር ደህንነት ላይ የሚመድቧቸው ሰዎች በሙያዊ ብቃትና ሥነ ምግባር ምሉዕ መሆን አለባቸው። በተጨማሪ የተቋማቱን ቴክኖሎጂ በየጊዜው ማዘመንና ኦዲት ማስደረግ ይጠበቅባቸዋል ብለዋል።

የሳይበር ደህንነትን የማስጠበቅ ሥራ የአንድ ተቋም ሥራ ብቻ ሊሆን አይችልም ያሉት ዶክተር ሹመቴ፤ ሁሉም አካላት በኃላፊነት መንፈስ በመሥራት ከሳይበር ጥቃት ደህንነታቸው የተጠበቀ ተቋማትን መገንባት አለብን ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል። ፡

ለአብነትም በኢትዮጵያ ብቻ በ2013 ዓ.ም የደረሰው የሳይበር ጥቃት ሙከራ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ መጨመሩንና በ2014 ዓ.ም ግማሽ ዓመት ላይም ከ3400 በላይ ከፍተኛ እና አደገኛ የሆኑ የሳይበር ጥቃት ሙከራዎች እንደተመከቱ ዶክተር ሹመቴ አንስተዋል።

እንደ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር መረጃ ከሆነ፤ የዲጂታል ሥነ ምህዳሩ ላይ የሚገቡና የሚወጡ ማናቸውም መረጃዎች ጤናማ ስለመሆናቸው ቁጥጥር ይደረግባቸዋል። የሳይበር ጥቃት የሚመስል መረጃ ከተገኘ የቅድመ መከላከል ዕርምጃ ይወሰዳል። ከዚያ አልፎ የሚመጣ ካለ ደግሞ የመልሶ ማጥቃት እርምጃ ይወሰዳል።

# ከ2 ሺህ በላይ ተፈናቃይ ተማሪዎች በድንኳን ውስጥ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ነው

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- በአሸባሪው ሕወሓት ወረራ የተፈናቀሉ ከሁለት ሺህ በላይ ተማሪዎች በድንኳን ውስጥ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ መሆኑን በአማራ ክልል ከዋግኽምራ ብሔረሰብ አስተዳደር ዞን ኮሙኒኬሽን መምሪያ አስታወቀ፡፡

የዞኑ ኮሙኒኬሽን መምሪያ ኃላፊ አቶ ከፍያለው ደባሽ እንዳስታወቁት፤ በአሸባሪው ሕወሓት ወረራ የተነሳ የተፈናቀሉት ተማሪዎቹ በአማራ ክልል የዋግኽምራ ብሔረሰብ አስተዳደር ዞን በወለህ የተፈናቃዮች መጠለያ ጣቢያ በድንኳን ውስጥ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ይገኛሉ።

ተማሪዎቹ አቅም በፈቀደ መጠን በየአካባቢው በሚገኙ ትምህርት ቤቶች የሚማሩበት ሁኔታ ተመቻችቶ ነበር፡፡ ነገር ግን የተፈናቃዩ ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱና ተፈናቃዩም ለትምህርት ቅበላ በማያመች መልኩ ዘግይቶ መቀላቀል በመጀመሩ ችግሩን ለመፍታት በድንኳን ትምህርት እየተሰጠ ይገኛል ብለዋል።

ትምህርት መምሪያው ባደረገው ጥረትና በተፈናቀሉ መምህራን ትብብር በተፈናቃዮች የመጠለያ ጣቢያዎች በድንኳን ትምህርት እንዲጀመር ተደርጓል ያሉት አቶ ከፍያለው፤ ከአበርገሌ፣ ከዝቋላና ከፃግብጂ ተፈናቅለው የመጡ መምህራን ያለምንም ተጨማሪ ክፍያ በመጠለያ ጣቢያው ተገኝተው እያስተማሩ መሆኑን ገልጸዋል።

የዕርዳታ ድርጅቶችም ለትምህርቱ መጀመር ድንኳኖችን በማቅረብ መተባበራቸው የሚያስመሰግን ተግባር መሆኑን ገልጸዋል። ፡

የዋግኽምራ ብሔረሰብ አስተዳደር ዞን ከአንድ ወረዳ በስተቀር ሁሉም ወረዳዎቹ በአሸባሪው ሕወሓት እጅ ገብተው እንደነበር ያስታወሱት አቶ ከፍያለው ፤ በወረራው በርካታ ትምህርት ቤቶች መውደማቸውንም ገልጸዋል።



ተፈናቃይ ተማሪዎች በድንኳን ውስጥ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ይገኛል

በደረሰው ወረራና ውድመት የተነሳ በዞኑ በሚገኙ አብዛኛዎቹ ወረዳዎች ላይ የመማር ማስተማር ሥርዓቱ ችግር ላይ ወድቆ ነበር። ይሁንና በተደረገው ጥረት የመማር ማስተማር ሂደቱ በተለያዩ አማራጮች እንዲቀጥል መደረጉን አስታውቀዋል።

በዚህም ከአበርገሌና ከፃግብጂ ወረዳ ውጪ ያሉ ወረዳዎች በሙሉ ቀደም ብለው መደበኛ ትምህርት በመግባታቸው ወደ ሁለተኛው መንፈቀ ዓመት ትምህርት ተሸጋግረዋል ብለዋል፡፡

በሌላ በኩል በአብዛኞቹ ወረዳዎች ያለው የተማሪ ቁጥር ከቀድሞው ማለትም በሰላሙ ጊዜ ከነበረው ጋር ሲነፃፀር ያነሰ መሆኑን ጠቁመው፤ በተለይ እንደ ዝቋላና ሰቆጣ ዙሪያ ወረዳ ላይ ባሉ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይህ የተማሪዎች ቁጥር መቀነስ ጎልቶ እንደሚታይ ኃላፊው ገልፀዋል፡፡

አቶ ከፍያለው ዝቋላ ወረዳን እንደ አብነት አንስተው ሲያስረዱ ቀድም በወረራው ጊዜ ስፍራው በሕወሓት ታጣቂዎች የተያዘ ነበር። አሁን አካባቢው ቢረጋጋም የተማሪ ወላጆች ግን የሰላሙ ሁኔታ አስተማማኝ አይደለም ብለው ስለሚያስቡ ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት አይልኩም ብለዋል፡፡

በተመሳሳይ ሰቆጣ ዙሪያም የሚገኝ አንድ ቀበሌ በሕወሓት እጅ ስለሆነ ወላጆች ልጆቻቸውን በፍርሃት ወደ ትምህርት ቤት መላክ አልቻሉም፤ እነዚህ ሁኔታዎች ተዳምረው የተማሪዎችን ቁጥር አነስተኛ እንዳደረጉት ተናግረዋል።

ይሁንና በዞኑ በሚገኙ የተለያዩ ቦታዎች ላይ የሚገኙ ተፈናቃይ ተማሪዎችን ለማስተማር የሚደረገው ጥረት ቀጥሏል። አማራጭ ያለውን በትምህርት ቤቶች በማስተማር በመጠለያ ጣቢያ የሚገኙትን ደግሞ በጊዜያዊ ድንኳኖች ውስጥም ትምህርት እንዲከታተሉ የሚደረገው ጥረት ቀጥሏል ብለዋል።

# የኢድ በዓል የጽንፈኞች ሴራ የከሸፈበት በዓል ሆኖ ማለፉን ክልሎች ገለጹ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- 1443ኛው የዒድ-አልፈጥር በዓል የጽንፈኞች ሴራ የከሸፈበት በዓል ሆኖ ማለፉን ክልሎች ገለጹ።

በየአካባቢው በሃይማኖት ሽፋን ግጭት ለመቀስቀስ የሚሞክሩ አካላት ላይ እርምጃ እንደሚወሰድ ክልሎች ትናንትና ባወጡት መግለጫ አስታውቀዋል።

የኦሮሚያ ክልል ባወጣው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ ጽንፈኞች የተለያዩ ሴራዎች በመፍጠር የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት እንዲሸረሸር ለማድረግ ቢሞክሩም ሕዝቡ እጅ ሳይሰጥ ባህሉን፣ እሴቱን እና ሃይማኖትን ጠብቆ በዓሉን አክብሯል።

የሃገሪቱ ጠላቶች ሃይማኖትን ከለላ በማድረግ በሰላም ተከባብሮ በሚኖር ሕዝብ መሐል መርዝ በመርጨት የጠላቶቻችን ሴራ ለማስፈጸም ጥረት እያደረጉ መሆኑን ጠቁሟል።

የሃገራችን ጠላቶች በዛሬው ቀን የኢድ አልፈጥር በዓልን ለማክበር በወጣው ሕዝብ ውስጥ በመደበቅ የውጭ አካላትን ዕኩይ ዓላማ ለማሳካት በአዲስ አበባ ከተማ ያደረጉት ሙከራ በሃይማኖቱ ተከታዮች እና በጸጥታ አካላት ብርቱ ጥረት እንዳልተሳካም ገልጿል።

መንግስትም ሴራን በሚጠነስሱ ጠላቶች ላይ ዕርምጃ በመውሰድ ላይ እንደሚገኝም ገልጾ፤ የጠላቶቻችንን ሴራ እያፈረስን የሃገራችንን ብልጽግና እውን ለማድረግ እንሠራለን ሲል ክልሉ አስታውቋል።

በተመሳሳይ የአማራ ክልል ባወጣው መግለጫ በክልል ለብዙ ሺህ ዓመታት ተከባብሮና ተቻችሎ በፍቅርና በአንድነት የኖሩትን የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖቶችን በማጋጨት የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት ከውጭና ከውስጥ የተደረገ ሴራ እንደሆነ አስታውቋል።

ጠላቶቻችን ከውጭም ከውስጥምበሚያደራጁትና በሚያቀነባብሩት ሴራ ተላላኪዎቻቸውን በገንዘብ በመደለል በመደበኛ ውጊያ ያልቻሉትን ሃገር የማፍረስ



እኩይ ዓላማቸውን በሃይማኖት ሽፋን ማባሪያ የሌለው ጥፋት መፈጸም ይፈልጋሉ ሲልም አስታውቋል።

በየትኛውም መንገድ የሕዝቡን ሰላምና አንድነት የሚያናጋ በሃይማኖትም ይሁን በሌላ ማናቸውም ዘዴ ግጭትን የሚሰብኩ፣ የሚቀሰቅሱና የጸጥታ መዋቅሩን ሥራ በሚያደናቅፉ አካላት ላይ የክልሉ መንግሥት እየወሰደ ያለውን ርምጃ አጠናክሮ ይቀጥላል ብሏል በመግለጫው።

የሶማሌ ክልል በበኩሉ የኢድ በዓልም በጽንፈኞች ሴራ ሳይደናቀፍ በሰላም ማለፉን አስታውቆ፤ ብሔርና ሃይማኖትን ሽፋን በማድረግ ሁከትና ብጥብጥ ለመፍጠር የሚሞክሩና በሕጋዊ ፖለቲካ ፓርቲ ሽፋን ለውጭ አካላት የሚላላኩ ኃይሎች ላይ ርምጃ እንደሚወስድ ገልጿል።

በተለይም ፅንፈኛ በሆኑ አካላት በሃይማኖት ሽፋን ከውጭ ኃይሎች ጋር በመሥራት ተዋልዶና ተጋብቶ በኖረ ሕዝብ መካከል ብጥብጥን ለመፍጠር እየተሠሩ ያሉትን የክልሉ መንግሥት ሕዝብ አጥብቆ የሚቃወም መሆኑን ጠቁሟል።

የአፋር ክልል በበኩሉ በየትኛውም ሃይማኖት ውስጥ በመመሸግ የራሱን ድብቅ አጀንዳ ለማስፈፀም የሚሞክርን፣ ግጭቶችን በመቀስቀስ አትራፊ ለመሆን የሚደረገውን ሩጫ ሕዝባችን ፈፅሞ እንደማይታገስ አስታውቋል።

የኢድ አል ፈጥር በዓል በሰላማዊ መልኩ መጠናቀቁን በማስታወስ፤ ሕዝቡ የተቸገሩን በመርዳት በተለይም በጁንታው ምክንያት ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉ ዜጎች ጋር በጋራ በመሆን ኢዱን እንዳሳለፈ በመግለጫው ተብራርቷል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በበኩሉ በመዲናዋ የኢድ ሰላት ወቅት ትርምስና ብጥብጥ ለመፍጠር ሙከራ ያደረጉ አካላት መኖራቸውን ጠቁሟል።

የዚህ እኩይ ተልእኮ ውጥን በሰማዕታት ሐውልትና በመስቀል አደባባይ በተደረገ ሙከራ በንብረትና በፀጥታ ኃይሎች ላይ መጠነኛ ጉዳት ቢያደርስም በሰላም ወዳድ ሙስሊም ወገኖቻችን ብርቱ ጥረትና በፀጥታ ኃይሎች ቅንጅት የትርምስ ፍላጎቱና ዕቅድ ሙሉ ለሙሉ ከሽፏል ብሏል፡፡

ጥፋተኞቹ ላይ መንግሥት የማያዳግም እርምጃ ለመውሰድ ሁኔታው ከተከሰተበት ሰዓት ጀምሮ አስፈላጊውን የማጣራትና የክትትል ሥራ በማከናወን ላይ መሆኑን አስታውቋል።

የሐረሪ ክልል በዓሉ በሰላምና በፍቅር መከበሩን ገልጾ፤ ሕዝቡን በማጋጨትና ክልሉን የሁከትና የጦርነት ማዕከል ለማድረግ በሚንቀሳቀሱ አካላት ላይ ሕጋዊ እርምጃ እንደሚወስድ አስታውቋል፡፡

በተመሳሳይ የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ የደቡብ ምዕራብ፣ የሲዳማ፣ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ የጋምቤላ ክልሎችና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ባወጡት መግለጫ የሴረኞችን ዓላማ ያከሸፈ በዓል መከበሩን አስታውቀዋል።

ኅብረተሰቡም ጽንፈኞችን የሚያራምዱትን ተልዕኮ ባለመከተልና በማጋለጥ የአገሩን ሰላም መጠበቅ እንዳለበት ክልሎች አሳስበዋል፡፡

# ወሕዴግ ሃገራዊ ምክክሩ ዕውን እንዲሆን የበኩሉን ለመወጣት ዝግጁ መሆኑን አስታወቀ

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡-ተስፋ የተጣለበት ሃገራዊ ምክክር ዕውን እንዲሆን የበኩሉን ሚና ለመወጣት ዝግጁ መሆኑን የወላይታ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ወሕዴግ) አስታወቀ፡፡


የወላይታ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ወሕዴግ) ሊቀመንበር አቶ ተክሌ ቦረና ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቆይታ እንዳስታወቁት፤ ፓርቲው ለሃገራዊ ምክክሩ ስኬታማነት የትኛውንም አይነት ዋጋ ለመክፈል ዝግጁ ነው፡፡

ሃገራዊ ምክክሩ ዕውን ሆኖ ችግሮች እንዲቃለሉ ፓርቲያቸው ፍላጎት እንዳለው ገልጸው፤ ለዚህ ስኬትም በግልም ሆነ በፓርቲ ደረጃ ማንኛውንም አይነት መስዋዕትነት ለመክፈል ቁርጠኝነቱ አለ ብለዋል።

አቶ ተክሌ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ከባዕዳን ጋር ካደረገችው ጦርነት በተጨማሪ ለበርካታ ዘመናት የእርስ በእርስ ጦርነትን አስተናግዳለች፡፡ የእርስ በእርስ ጦርነቱን የመጣው ደግሞ እርስ በእርስ መግባባት ባለመቻላችን ነው፡፡ በቀጣይ ሊካሄድ የታቀደው ሃገራዊ ምክክርም ይህን ችግር አስወግዶ መግባባትን እንደሚፈጥር ይታመናል።

ንጹሕ አየር እየተነፈሱ የልማት መሠረት የሆነውን ሠላምን መገንባትና አስተማማኝ ልማትን ማራመድ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህ ስኬት ሃገራዊ መግባባቱ ወሳኝነት አለው። ለምክክሩ ሂደት መሳካትም ወሕዴግ የድርሻውን ይወጣል ሲሉ አስታውቀዋል።

ዜጎች የተደላደለ ሕይወት እንዲኖሩ የሚያስችል



አቶ ተክሌ ቦረና

ሃገር ለመፍጠር አለመግባባቶች መፈታት አለባቸው ያሉት አቶ ተክሌ፤ ብረት አንስተው ጫካ የገቡ እንዲሁም የተለያየ ርዕዮተ ዓለም መርጠው ጽንፈኝነትን የሚያቀነቅኑም አሉ። ነገር ግን ችግሮችን መፍታት የሚቻለው በጦርነትና በአለመግባባት ሳይሆን በሃገራዊ የምክክር መድረክ ነው ብለዋል።

የብሔራዊ መግባባት ጽንሰ ሀሳብ ለበርካታ ዓመታት በመፈክርነት ተይዞ የቆየ ጉዳይ መሆኑ አቶ ተክሌ አስታውሰው፤ በተለይ ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ላለፉት በርካታ አስርት ዓመታት ይሄንን ሀሳብ ሲያራምዱ እንደነበር ገልጸዋል።

አሁን ላይ ጊዜው ፈቅዶና መንግሥትም አምኖበት ለሃገራዊ ምክክር ዝግጅት መደረጉ ችግሮቻችንን ለመፍታት ትልቅ ተስፋ የሰነቀ ሆኗል ብለዋል።

ተስፋው ዕውን እንዲሆን በሃገራዊ ምክክሩ የአገሪቷ ችግር ምን እንደሆነ፣ ለምን ዜጎች እንደሚሰቃዩ፣ በጥልቀት በማየት ችግሮችን መለየት እንደሚገባ አቶ ተክሌ ተናግረዋል፡፡

አጀንዳዎቹ የችግሮችን ምንነት ነቅሶ በማውጣትና መግባባትን መሠረት ያደረጉ እንዲሆኑ በማስቻል ላይ የምክክሩን ውጤታማነት ማሳደግ እንደሚገባም ገልጸዋል።

ፖለቲካ ፓርቲዎች ቅሬታ ተሰምቶናል ብለው ቢያፈነግጡ ውጤቱ ጥሩ እንደማይሆን ገልጸው፤ በሌሎች አገሮች የታዩ አገር አፍራሽ ተግባሮች በኢትዮጵያም እንዳይከሰቱ ከጽንፈኝነትና ከጎጠኝነት በራቀ መንገድ በምክክሩ ተሳትፎ ማድረግና ለውጤታማነቱም ዝግጁ መሆን እንደሚጠበቅባቸው ጠቁመዋል፡፡

ከዚህ አኳያ ፓርቲዎች ጽንፍ በረገጠ አካሄድ ከመዝለቅ ይልቅ በመግባባት ላይ በተመሠረተ አካሄድ በመሳተፍ ምክክሩ እንዲሳካ ጥረት ማድረግ ይገባቸዋል ብለዋል።

አቶ ተክሌ እንዳስታወቁት፤ የአገራዊ ምክክሩን ዓላማ የሚያበላሽ ነገር በምንም አይነት ሁኔታ መፈጠር የለበትም፡፡ ለዚህም እያንዳንዱ ፓርቲና ግለሰብ ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል።



አቶ ቶሎሳ ተስፋዬ

# ጽንፈኛና አሸባሪ ኃይሎች ላይ ተመሳሳይ አቋም መያዝ እንደሚያስፈልግ ተጠየቀ

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- የሕዝቡን ሰላም በማወክ የአገር ህልውና እያፈኑ ያሉ ጽንፈኛና አሸባሪ ኃይሎች ላይ ተመሳሳይ አቋም መያዝ ያስፈልጋል ሲሉ ፖለቲከኛና የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አማካሪ አቶ ቶሎሳ ተስፋዬ ተናገሩ።

አቶ ቶሎሳ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ አሁን ላይ የዜጎች የመኖር ዋስትና በጽንፈኞችና በአሸባሪዎች ሴራ አደጋ ላይ ወድቋል። ለዚህም በሁሉም አካባቢ ተመሳሳይ አቋም በመያዝ እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል።

ጽንፈኞችና አሸባሪዎች የግላቸውን ፍላጎት በኃይል ለማሟላት ልማት ከማስተጓጎል፣ሕዝብና ሃገር ከማሸበር በዘለለም ለየትኛውም ወገን ጠቃሚ አለመሆናቸው ከአገራችንና ከዓለም ተሞክሮ በቀላሉ መረዳት ይቻላል ያሉት አማካሪው፣ ማንንም የማይጠቅሙትን የጥፋት ኃይሎች በሁሉም አካባቢ ተመሳሳይ አቋም ተይዞ ዕርምጃ ካልተወሰደ የሚያስከትሉት መዘዝ የማንወጣው ይሆናል ብለዋል።

ብሔራዊ ደህንነት ምክር ቤት ሰሞኑን የዜጎችን ደህንነት አስመልክቶ ያወጣው መግለጫ ቢዘገይም ተገቢ ነው፤ ሰው እየተገደለ፣ንብረት እየወደመ፣ልማት እየተስተጓጎለ በጥቅሉ የሰላም መድፍረስ እየተባባሰ መምጣቱን በማመን ምክር ቤቱ መግለጫ ማውጣቱ የሚደገፍ ድርጊት መሆኑን ገልጸዋል።

መንግሥት ሕዝቡን በማስተባበር በየትኛውም አካባቢ የሚንቀሳቀሱ ጸረ ሰላም ኃይሎች ለአንዴና ለመጨረሻ አደብ ለማስያዝ አስፈላጊውን መስዋዕትነት ለመክፈል ቁርጠኛ መሆን ይጠበቅበታል። ዕርምጃውም በተግባር መደገፍ አለበት ብለዋል።

እንደ አቶ ቶሎሳ ማብራሪያ፤ ጽንፈኞችና አሸባሪዎች በየክልሎቹ ብቅ ብቅ ማለት ከጀመሩ ሰንበትበት ብለዋል። በእነዚህ ቡድኖች በየጊዜው የሚፈጠሩ ግጭትና የሰላም እጦት ውስጥ አገራዊ ምክክር ማካሄድ አጠያያቂ ነው።

መንግሥት ቡድኖቹን ለማጥፋት ከባድ መስዋዕት እየከፈለ መሆኑ ሲናገር ይደመጣል። ነገር ግን ሕዝቡ እየከፈለ ላለው መስዋዕትነት ጋር ሲነጻጸር እምብዛም አይደለም። ያም ሆኖ የሸብር ቡድኑ ጥፋት አሁንም ባለበት ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ጽንፈኛም ሆነ የአሸባሪ ኃይሎች በዋናነት የሚጎዱት የገዛ ወገኖቻቸው አለፍ ሲል ደግሞ ሃገራቸው መሆኑ የማይካድ ሐቅ ነው ያሉት አቶ ቶሎሳ፣ከዚህ አንጻር የሸኔ ሽብር ቡድኖች በግንባር ቀድምትነት የኦሮሞ ሕዝብ በተለይ ባለፉት ሶስት ዓመታት የኢኮኖሚ እንቅስቃሴውን በመግታት ለከፋ ችግር እንዲዳረግ አድርጓል ብለዋል።

በተጨማሪ አሸባሪ ቡድን ለበርካታ ሰዎች ሞትና ለንብረት ውድመት ምክንያት መሆኑንም አመልክተዋል።

የኦሮሞ ሕዝብ በተለይ አርሶ አደሩ አርሶ ወይም ነግዶ መደበኛ ኑሮውን መምራት ተስኖታል ያሉት አማካሪው፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በምስራቅና በምዕራብ ሸዋ፣በምስራቅ ወለጋ ጽንፈኞች ሕዝቡ ላይ የፈጸሙት በደል አሳዛኝ መሆኑን ጠቁመው፤ አሁን ላይ በኦሮሚያ ሕዝቡ ሸኔንና ጽንፈኞቹን እንደሚያወግዝ ሁሉ በሌሎች ክልሎችም በተመሳሳይ መልኩ ጸረ ሰላም ኃይሎች ላይ ወጥ አቋም መያዝ አለበት ብለዋል።

# ክርስቲያን ሙስሊሙ በሰላም የሚሳተፍበትን እንደ ኢፍጣር ያሉ መርሐ ግብሮችን ማስተዋወቅ ያስፈልጋል

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- ስለኢትዮጵያ የሚወራውን መጥፎ ዜና ለማረቅ ክርስቲያን ሙስሊሙ በሰላም የሚሳተፍበትን እንደ ኢፍጣር ያሉ መርሐ ግብሮችን በአግባቡ ማስተዋወቅ ይገባል ስትል በአሜሪካ ዳላስ የቢላል ኮሚዩኒቲ አባል የሆነችው ሃናን መሐመድ ተናገረች።

ከኢድ እስከኢድ አገራዊ ጥሪን ተከትሏ ወደኢትዮጵያ የመጣችው ሃናን መሐመድ በአሜሪካ ዳላስ ቴክሳስ ነዋሪ ስትሆን፤ ከ13 ዓመት በኋላ ወደአገሯ መመለሷን ትገልጻለች።

ወደአገሯ ከገባች በኋላም ብዙ መጥፎ ጉዳዮችን ብትሰማም እነደኢፍጣር ያሉ ክርስቲያን ሙስሊሙ በሰላምና በፍቅር የሚታደምበት መርሐ ግብር ላይ መሳተፍ መቻሏን ተናግራለች።

ሰባት ወር የሆናት የታናሽ እህቷን ልጅ ይዛ በአዲስ አበባ ታላቁ የጎዳና ላይ ኢፍጣር መርሐ ግብር ላይ በሰላም መሳተፏን ገልጻ፤ በዚህም ዝግጅት በውጭው ዓለም የማይዘወተረውን ልምድ መካፈል በመቻሏ ደስተኛ መሆኗን ገልጻለች።

ይህን አይነቱን መርሐ ግብር በዓለም ደረጃ በማስተዋወቅ ለቱሪዝም መስህብነትም መጠቀም እንደሚገባ መልዕክት አስተላልፋለች።

እንደ ሃናን ገለጻ፤ ኢትዮጵያውያን ያለንን በጎ ልምድና መልካም ነገር ሳይሆን መጥፎ መጥፎው ላይ ነው ትኩረት የምናደርገው ፤ ይህ አይነቱ አካሄድ መቀየር



ፎቶ - አዮብ ተፈሪ

ወጣት ሃናን መሐመድ

አለበት። በውጭው ዓለም ያለውን ልምድ በመውሰድ የእራስን በጎ ነገር መሸጥ ላይ ማተኮር ይገባናል።

በተለይ ወቅትን ጠብቀው የሚከሰቱና ሕዝብ በብዛት የሚታደምባቸውን ዝግጅቶቻችንን በማስተዋወቅ ጎብኝዎች እንዲመጡ ማድረግ ይቻላል የምትለው ሃናን፤ የጎዳና ላይ ኢፍጣር መርሐግብሩንም በተለይ ለዓረቡ ዓለምና ለሩቅ ምስራቅ ዜጎች በማስተዋወቅ ጥሩ የቱሪዝም ገቢ መፍጠር እንደሚቻል ነው የጠቆመችው።

የጎዳና ላይ ኢፍጣር መርሐ ግብሮች በየከተሞቹ እንደሚደረጉ መረጃዎች ያሳያሉ፤ በተለያዩ አካባቢዎች የሚደረጉት የኢፍጣር ሥነሥርዓቶች ከአክራሪነትና በጽንፈኝነት አካሄድ በተለየ መንገድ በፍቅርና በሰላም የሚከናወኑ ናቸው። ይህ በእራሱ ልዩ የሆነ ስሜትን የሚሰጥ አብሮነትንና ሰላምን የሚሰብክ አጋጣሚ በመሆኑ በሚገባ ልንጠቀምበት ይገባል ብላለች።

በየክልሉ የሚገኙ የቱሪዝም ቢሮዎችም ሆነ የፌዴራል መንግሥት እንዲሁም በአስጎብኚነት የሥራ ዘርፍ ላይ የተሰማሩ አካላት ሁሉ የተገኘችውን በጎ አጋጣሚ በመጠቀም የቱሪስት መስህብ ለማድረግ ጥረት ማድረግ አለባቸው ስትልም ገልጻለች።

በዚህ ረገድ የጎዳና ላይ ኢፍጣር መርሐ ግብሮችን በይበልጥ የአብሮነትና የመተሳሰብ ስሜታቸውን እንዲጎለብት በማድረግ ይገባል የምትለው ዲያስፖራዋ፤ መርሐግብሮቹን በአግባቡ በማስተዋወቅ ስለኢትዮጵያ የሚወሩትን መጥፎ መጥፎ ዜናዎችና መረጃዎች የሚያደርሱትን አሉታዊ ተጽእኖን መቀነስ ይቻላል ስትል አስረድታለች።

ዜጎች በሰላምና በአንድነት ተከባብረው የሚያከብሩት ሥነሥርዓት መሆኑን ለዓለም በማስተዋወቅ ስለኢትዮጵያ በጎ በጎው እንዲወራ እድል የምንፈጥርበት አጋጣሚ በመሆኑ በየዓመቱ በጉዳዩ ላይ ተገቢውን የቱሪዝም ሥራ ማከናወን ይገባል ስትል መልዕክቷን አስተላልፋለች።

## በጠላቶች ሴራና...

ከገፅ 1 የዞረ

ትስስሮቻችንን ለመበጣጠስ፤ በሃገራችን ውስጥ አስተማማኝ ሰላምና መረጋጋት እንዳይሰፍን ለማድረግ እንዲሁም ከአንድነት ይልቅ መበታተንና መከፋፈል እንዲፈጠር አልመው እየሠሩ መሆኑን ገልጿል።

ከሰሞኑ በአማራ ክልል ጎንደር ከተማ ካጋጠመው ረብሻ ጋር ተያይዞ ግጭቱን ወደ ደቡብ ክልል ወራቤ ከተማና ወደ ሌሎች አካባቢዎች በማስፋፋት ሁከትና ብጥብጥ እንዲፈጠር ሙከራ ማድረጋቸው ያስታወሰው መግለጫው፥ በማኅበራዊ ሚዲያዎች ሰሞኑን የፀረ-ኢትዮጵያ አቋሞቻቸውን በመግለፅ ቀጣይ ሊፈጥሩት ስላሰቡት ሁከት በአደባባይ ሲገልፁ ሰንብተዋል ብሏል፡፡

ይህንኑ እኩይ ዓላማቸውን በዛሬም በአዲስ አበባ የታላቁ ዒድ ሰላት ላይ ለመተግበር ሙከራ ቢያደርጉም በንብረት እና በፀጥታ ኃይሎች ላይ ከደረሰው መለስተኛ ጉዳት ውጭ ምንም አይነት ጉዳት ሳይደርስ በሰላም ወዳድ አማኞችና በፀጥታ ኃይሎች ቅንጅት የትርምስ ፍላጎቱና ዕቅዱ መክሸፉን ገልጿል።

ታሪካዊ ጠላቶቻችን ኢትዮጵያን ለማተራመስና ለማፍረስ እንደ መሣሪያ ከሚጠቀሙባቸው ጉዳዮች ውስጥ የለውጥ ሂደቱ ፈተና ሆነው የቀጠሉት የሃይማኖት ፅንፈኝነት፣ አክራሪነትና መንደርተኝነት ዋነኞቹ መሆናቸውን ጠቁሟል።

በዚህም በፈጠሩት ችግር በሰማዕታት ሐውልትና በመስቀል አደባባይ በንብረት እና በፀጥታ ኃይሎች ላይ ከደረሰው መለስተኛ ጉዳት ውጭ የተለየ ጉዳት ሳይደርስ በሰላም ወዳድ አማኞችና በፀጥታ ኃይሎች ቅንጅት የትርምስ ፍላጎቱና ዕቅዱ ከሽፏል ብሏል፡፡

በቀሪዎቹ የሃገሪቱ አካባቢዎች የ1443ኛው የታላቁ የኢድ አልፈጥር በዓል ሰላት በደማቅ ሁኔታ ተካሂዶ በሰላም መጠናቀቁን አስታውቋል።

መላው ሕዝባችን የታሪካዊ ጠላቶቻችንና በውስጣችን የሚገኙ የተላላኪዎቻቸውን እኩይ ሴራዎች ተገንዝቦ ፅንፈኝነትንና መገፋፋትን በቁርጠኝነት በመታገል ሕብረ ብሔራዊ አንድነቱን ማረጋገጥ አለበት ሲል መንግሥት ገልጿል።

መንግሥት በፅንፈኞች ላይ የሚወስደውን እርምጃም አጠናክሮ ይቀጥላል ያለው መግለጫው፤ በየትኛውም የሃገሪቱ አካባቢዎች በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ሃይማኖትን ሽፋን በማድረግ እንዲሁም በሌሎች መንገዶች ሁከትና ብጥብጥ ለመፍጠር የሚንቀሳቀሱትን አካላት አንድ በአንድ በመልቀም የጀመረውን ሕግና ሥርዓት የማስከበር እንቅስቃሴ አጠናክሮ ይቀጥላል ብሏል።

ይህንን ተግባር ለመፈፀም መንግሥት ሙሉ ቁርጠኝነትና ጠንካራ አቅም እንዳለው አሳውቋል።

አብዛኛው ሰላም ወዳድ የዕምነቱ ተከታዮች በዓሉ በተረጋጋና በሰከነ ሁኔታ እንዲካሄድ ያደረጉት ተሳትፎና ከፀጥታ አካላት ጋር አብሮ ለመሥራት ያሳዩት ተነሳሽነት በእጅጉ የሚደነቅና የሚበረታታ ነውም ብሏል በመግለጫው።

መላው ሕዝባችን የታሪካዊ ጠላቶቻችንና በውስጣችን የሚገኙ የተላላኪዎቻቸውን እኩይ ሴራዎች ተገንዝቦ ፅንፈኝነትንና መገፋፋትን በቁርጠኝነት በመታገል ሕብረ ብሔራዊ አንድነቱን ማረጋገጥ አለበት ሲል መንግሥት መልዕክት አስተላልፏል።

ዘመን የማይሽረውን የሕዝባችንን አንድነትና መተባበር በማጎልበት ሁሉም ሰው ያለ ልዩነት ሃይማኖትን፣ ብሔርንና መንደርተኝነትን ማዕከል ያደረገውን አክራሪነትና ፅንፈኝነትን የመወጋት ዘመቻን በፅናት መቀጠል እንዳለበት ተገልጿል።

መንግሥት እንዳስታወቀው፤ በታሪካዊ ጠላቶቻችን ሴራና በውስጣዊ ባንዳዎች ተባባሪነት ኢትዮጵያን የማተራመስ እኩይ ውጥን መቼም ቢሆን አይሳካም።

## በሃይማኖት ሽፋን...

ከገፅ 1 የዞረ

ሃገር የሚመጥኑ አይደሉም:: ለየትኛውም ሐይማኖት ተከታይም እንደዚህ ዓይነት ነውር ነገሮችን መፍጠር ተገቢ አይደለም::

ድርጊቱ ሊወገዝ የሚገባው ተግባር ነው ያሉት አቶ አራጌ፤ ለወደፊቱም ተፋቅረን፣ ተዋደን እና ተጋግዘን ልንኖር መቻል አለብን ብለዋል::

ጥፋን በጥፋት መመለስ የማይደገፍ ተግባር ነው፤ በመሆኑም ኢትዮጵያ ሰከን ብለው የሚያስቡ ሕዝቦችና የሃይማኖት እኩልነትን የምታከብር ሃገር አድርገን ልንገነባት ይገባል:: ለዚህ ደግሞ ሃይማኖትን ተገን በማድረግ የሚንቀሳቀሱ አጥፊዎች በሕግ መጠየቅ አለባቸው ብለዋል::

ሼህ መከተ ሙሄ በበኩላቸው፤ በሃገራችን የተለያዩ አካባቢዎች ሃይማኖትን ሽፋን በማድረግ የተፈፀሙ ተግባራት እጅግ የሚያሳዝኑ ናቸው፤ ከአባቶችም ሆነ ከሃይማኖት መሪዎች አስተምህሮ ወጣ ባለ መልኩ በሃይማኖት ተከታዮች ላይ የሚወሰዱ ጥቃቶች እንደሚወገዙ ገልፀዋል::

ድርጊቱ ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ ያለችበትን አንፃራዊ ሰላምና መረጋጋት የሚንድ ስለሆነ ቶሎ ሊታረም የሚገባው ተግባር እንደሆነም አመልክተዋል::

መንግሥት ይህንን ችግር በፍጥነት እልባት መውሰድ እንደሚኖርበትና የተሳሳቱትን መክሮ መመለስ፤ አጥፊዎች በሕግ ፊት እንዲጠየቁ ማድረግ የሚጠበቅ ተግባር መሆኑንም ተናግረዋል::

ሙስሊሙም ሆነ ክርስቲያኑ ማኅበረሰብ እንደ አንድ ቤተሰብ አብሮና ተቻችሎ የኖረ ነው ይህ መልካም ተግባር በማስቀጠል ተከባብሮና ተቻችሎ መቀጠል ይኖርብናል ብለዋል ሼህ መከተ::

በኢትዮጵያ ውስጥ የሌላውን መብት መግፋትና አላግባብ ድርጊቶችን መፈፀም እጅግ አሳፋሪና ከኢትዮጵያውያን ያልወረስነው ዕሴት ነው ብለዋል::

እንደ ሼህ መከተ ገለፃ፤ የመገፋፋት፣ የመጠፋፋትና ዕውቅና ያለመስጠት ዕሴት ዕጅግ አደገኛ እና ሕዝቡንም ሃገርንም የሚጎዳ በመሆኑ ልንጠነቀቅ ይገባናል:: መንግሥትም ዋናው ተግባሩ የዜጎችን ሰላምና ደህንነት ማረጋገጥ እንደመሆኑ ይህንን ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል::

ያጠፉ ሰዎች ለሕግ መቅረብ አለባቸው ያሉት ሼህ መከተ፤ የተጎዱ ሊካሱ፤ ቤተሰባቸውን በሞት የተነጠቁም ሊፅናኑ ይገባልም ብለዋል::

እንደ ሼህ መከተ ፍትሕ ሊቆም የሚችለው የተስማማንበትን ሕግ በመካከላችን ስንተገብረው ነው:: መንግሥት እንደ መንግሥት ኃላፊነቱን ለመወጣት በሚተገብራቸው ተግባራትም ሕዝቦች አብረውት ሊቆሙ ይገባል::

አቶ ኢብራሂም ከድር በበኩላቸው የሃይማኖት ተከታይ ነን የሚሉ ሰዎች ከሃይማኖቱ ትዕዛዛት ውጪ የሚፈፅሙት ተግባር ተቀባይነት እንደሌለው ተናግረዋል::

ይህ ተግባር አንድነትን የሚያፈርስና ለረጅም ዓመታት ተከባብሮ የኖረውን ማኅበረሰብ የሚሸረሽር ነው ያሉት አቶ ኢብራሂም ችግሩን ማስተካከል ያለባቸው የሃይማኖት መሪዎች፣ አባቶችና መንግሥት የመጨረሻ ዕልባት ላይ እስኪደርስ ትኩረት ሰጥተው ሊሠሩበት ይገባል ሲሉ አሳስበዋል::

እንደ አቶ ኢብራሂም፤ ሃይማኖትን ተገን አድርገው የሚንቀሳቀሱ ሰዎችን ማጋለጥ ይገባል መንግሥትም አጥፊዎችን ለሕግ አቅርቦ ተጠያቂ ሊያደርግ ይገባል ብለዋል::

## ኢትዮጵያ የፍቅር...

ከገፅ 1 የዞረ

ሁሉም ለሰላም መቆም አለበት:: አለመግባባቶች በውይይትና በመግባባት ሊፈቱ ይገባቸዋል፤ ፈጣሪ በቃችሁ እንዲለን እንለምናለን ብለዋል ሼህ ሱልጣን::

ምክር ቤቱ አለመግባባቶች ሲፈጠሩ በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ ጥረት ማድረጉን በመጠቆምም፤ በትምህርት ቤቶች አካባቢ በተለያዩ ጊዜያት እያገረሹ ያሉ ችግሮችን ፈትሾ ከስር መሠረቱ እንዲፈቱ መደረግ እንዳለበትም አሳስበዋል::

በጎንደር፣ በደባርቅና አካባቢዎቹ የተከሰቱ መስጊዶችን ኢላማ ያደረጉ ጥቃቶችን ምክር ቤቱ አጥብቆ ይቃወማል፣ ያወግዛል ያሉት ሼህ ሱልጣን፤ በአገር ሰላም እንዲሰፍን ከተፈለገ መንግሥት በድርጊቱ የተሳተፉ አካላትን ለይቶ የማያዳግም ርምጃ ወስዶ በፍጥነት እንዲያሳውቅ አሳስበዋል::

በአዲስ አበባ ከተማ የሚሰገዱት ሁለት የኢድ ሰላቶች በመካና በመዲና ከሚሰገዱት ሰላቶች ቀጥሎ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሰጋጅ ከሚገኝባቸው የዓለም ታላላቅ የኢድ ሰላቶች መርሐ ግብር እንደሚመደብ አስታውሰዋል::

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ተቀዳሚ ሙፍቲ ሐጅ ዑመር እድሪስ በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ አንድ ሰው ሳይበላ ሳይጠጣ አይኖርም፤ በተመሳሳይም ያለሰላም ያለአንድነት፣ ያለልማት፣ ያለዕድገት፣ ያለመተባበር፣ ያለመከባበር፣ ያለመቀራረብ መኖር አይቻልም ብለዋል::

እርስ በእርስ አንገዳደል፣ የንጹሐን ደም አይፍሰስ፣ ሰዎች አይፈናቀሉ፣ ደም አይፍሰስ:: ይህ የሰው ጸባይ አይደለም:: ይህንን ባህሪ አጥፍተን ወደ ሰው ባህሪ እንመለስም ብለዋል::

በመሆኑም አንድነት፣ ሰላም፣ ልማት፣ ዕድገት፣ ራስን መቻል አስፈላጊ ናቸው:: ሙስሊሙ ልመና አዋራጅ ተግባር መሆኑን በመገንዘብ ሊቆጠብ እንደሚገባ መክረዋል:: አንድነት የሚገኘውና ሰላም የሚሰፍነው በተግባር እንደመሆኑ እያንዳንዱ ወደ ሰላምና ልማት መመለስ እንደሚገባውም መክረዋል::

ከኢድ እስከ ኢድ ጥምር ኮሚቴ ሰብሳቢ ኡስታዝ አቡበከር አሕመድ፤ ‹‹አንድነታችን እንዲጠነክር በመከባበር፣ በመተሳሰብ፣ በሰላምና የጋራ ኃላፊነትን በመወጣት መመላለስ ይገባናል›› ሲሉ ተናግረዋል:: በጎንደር የደረሰው ፈተና አንገታችንን አስደፍቷል፣ ልባችንን ሰብሯል፣ ውስጣችንንም አድምቷልም ብለዋል::

እንደርሳቸው ገለጻ፤ ክፋትን በክፋት፣ ጥፋትን በጥፋት ለመመለስ የታዘዝን ሕዝቦች አይደለንም:: እያንዳንዱ ነገር ፍትሐዊነት በተሞላበትና ሌሎችን በማይነካ መንገድ መከናወን ይገባዋል:: የጥፋት ተምሳሌት የሆኑ አካላት ተምሳሌታችን አይደሉም:: ማንነታችን መልካምን መመለስ ነው::

በወንድሞቻችን፣ በዜጎች በማንነታችን ላይ የመጣ አደጋ ነው:: መንግሥት በወንጀል ድርጊቱ የተሳተፉ፣ የሰውን ነጻነት የገፈፈ፣ የእምነት ቦታዎችን ያረከሰ በማንነት ላይ የተቃጣውን ተግባር የፈጸሙ አካላትን በመለየት አፋጣኝና የማያዳግም ርምጃ ወስዶ ለሕዝብ ሊያሳውቅ ይገባልም ነው ኡስታዝ አቡበከር ያሉት::

የአዲስ አበባ ከተማ ብልጽግና ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ መለስ አለሙ፤ እስልምና መነሻውም መድረሻውም ሰላም ነው:: የኢድ በዓል የመተሳሰብና የመከባበር እንደመሆኑ በረመዳን ወቅት ካላችሁ በማካፈል ያሳያችሁት መልካም ተግባር በዘላቂነት እንደሚቀጥል ተስፋ አለኝ ሲሉ ተናግረዋል::

የቀደመውን አብሮነት የበለጠ ማሰብ ይገባል:: ሙስሊምና ክርስቲያን በጋራ የኖረባት አገር ናት:: ኢትዮጵያን የሠራናት መከራዋን የተጋራነውም በጋራ ነው:: ታሪካችን መዝገቡ ሲገለጥ የሚነበበው እውነታም ይኸው ነው ብለዋል አቶ መለስ::

ጠላትን ማሸነፍ የሚቻለው በአብሮነት ነው:: የጠላት ተልዕኮ በጋራ በመቆም ማሸነፍ ይገባል:: በማንነትና በሃይማኖት በመከፋፈል የራሳቸውን ፍላጎትና ጥቅም ማስፈን ነው፤ ከእዚህ ሙስሊምም፣ ክርስቲያንም፣ ኢትዮጵያም አያተርፉም::

አትራፊዎቹ የግጭት ተልእኮ ያላቸው ብቻ ናቸው:: በቃችሁ ልንላቸው ይገባል:: የቤታችንን ሰላም በጋራ እንጠብቅ ብለዋል::

# ርዕሰ አንቀፅ

## ጥቂቶች በዝተው እንዲያውኩ እድል መስጠት አይገባም

ኢትዮጵያውያን ከጥንት እስከዛሬ ተፈትነዋል፤ ፈተናቸውን ግን በድል ተሻግረዋል። ይህ ተፈትኖ የማለፍ ምስጢሩ ደግሞ ከልብ የሆነ አንድነት፣ ወንድማማችነትና ፍቅር ነው። ይህ የሰው ልጆች እውነተኛ ገጽ፤ የኢትዮጵያውያን ዘመን ተሻጋሪ ታሪክ፣ የማንነትና ብዝሃነታቸው መገለጫ የዓለም ተምሳሌታዊ ስማቸው ነው። ይህ እውነተኛ የኢትዮጵያውያን ማንነት ነው፤ በፈተና እንዳይሸነፉ፤ በሴራ እንዳይጠለፉ፤ በእኩያን ትርክት እሴታቸውን እንዳይሸረሽሩ አድርጎ ዘመን ያሻገራቸው፡፡

ይሁን እንጂ ትናንትም ሆነ ዛሬ ኢትዮጵያን ከፍ ያደረጉ ሕዝቦቿን ዝቅ ለማድረግ ብዙዎች ለፍተዋል፤ ጦር ሰብቀው ድንበር ጥሰው ገብተው ተዋርደው ተመልሰዋል፤ ሲሻቸው ማንነትን፣ ሲሻቸው ሃይማኖትን ተገን አድርገው ሊከፋፍሉና ሊያዳክሟቸው በብርቱ ጥረዋል፤ ለዚህም በብዙ መልኩ ሃብት፣ ጉልበት አፍስሰዋል። ይህ ሁሉ ሴራና ሃብት ግን ኢትዮጵያን ሊያወርዳት፤ ኢትዮጵያውያንንም ከፋፍሎ ሊያዋርዳቸው አልቻለም። ምክንያቱም ብዝሃነቱ እንዳይፈርስ በኢትዮጵያዊነት ታላቅ ገመድ ተዳውሮ ተሸምኗልና ነው፡፡

ይህ የብዙሃኑ እሴት ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ በጥቂት ብልጣብልጦችና የሴራ ተላላኪ ቅጥረኛ የሃይማኖትም ሆነ የብሔር ካባ ለባሾች ሲፈተን ማየቱ እየተለመደ መጥቷል። በተለይ ከለውጡ ማግስት እየተቀጣጠለ የመጣው አንድነትና ሕዝባዊ ወንድማማችነት የኢትዮጵያን የብልጽግና መንገድ በእጅጉ የሚያፋጥነው መሆኑን የተገነዘቡ የውስጥም የውጭም ኃይሎች ኢትዮጵያውያንን እርስ በርስ ለመከፋፈልና ለማባላት የሚያስችላቸውን አጀንዳ ቀርጸውን ሃብት መድበው በተላላኪ ቅጥረኞች አማካኝነት ቀን ከሌት እየተጉ መሆናቸው የአደባባይ ምስጢር ሆኗል፡፡

በቅርቡም በጎንደር፣ በወራቤ እና ሌሎችም አካባቢዎች የተገለጠው የእነዚሁ ኃይሎች እኩይ ሴራ እንጂ የአብሮ ኗሪው ሕዝብ (ክርስቲያኑም ሆነ ሙስሊሙ) አለመሆኑ የታወቀ ነው። ይሄን ተከትሎ የሚራገቡ ወሬዎች፤ የሚሰራጩ የጥፋት ቀስቃሽ መልዕክቶችና ሌሎችም የውጭም ሆነ የውስጥ ጉዳይ አስፈጻሚ የጥፋት ኃይሎች እና ግብራበሮቻቸው እንጂ የብዙሃኑን አማኝ ስሜትና ፍላጎት የተሸከሙ አልነበሩም። ከኢድ እስከ ኢድ ታላቅ የአገር ቤት ጉዞ ጥሪን ተከትሎም ሁነቱ እንዳይሳካ ለማድረግ እነዚሁ ኃይሎች በብርቱ ሲሰሩ መቆየታቸው ይታወቃል፡፡

ከኢድ አፍጥር እንዲሁም ከኢድ ታላቁ ሶላት መርሐ ግብር ጋር በተያያዘም በብዙ መልኩ መርዛማ መልዕክቶቻቸውንና አስተሳሰቦቻቸውን በብዙሃኑ ለማስረጽ ተግተው ቀስቅሰዋል። የአፍጥር መርሐ ግብሩ ላይ ያልተሳካላቸውን በሶላት መርሐ ግብሩ ለማስፈጸምም በብርቱ ለፍተዋል። የሚፈልጉት ባይሰምርላቸውም በጥቂቱም ቢሆን ግርግር ለመፍጠር ሞክረዋል። ሆኖም ትልቁ የብዙሃኑ ፍላጎት እንጂ የጥቂቶች ፍላጎት መቼም ቢሆን የሚሳካ አይደለምና ሕልማቸው በአጭር ተቀጭቶ ሴራቸው ከሽፏል። የእስልምናን የሰላም ገጽ ለማጠልሸት የሸረቡት እኩይ ዓላማ እንደ ጉም ተኖ ጠፍቶባቸዋል፡፡

በእለተ ኢድ በአዲስ አበባ የተፈጸመውን ይሄን የእኩያን የሴራ ተግባር ተከትሎ "በታሪካዊ ጠላቶቻችን ሴራና በውስጣዊ ባንዳዎች ተባባሪነት ኢትዮጵያን የማተራመስ እኩይ ውጥን በፍፁም አይሳካም!" ሲል የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ባወጣው መግለጫ እንዳመለከተውም፤ በአብዛኞቹ የኢትዮጵያ አካባቢዎች የ1443ኛው ኢድ አልፈጥር በዓል ሶላት በደማቅ ሁኔታ በመካሄድ በሰላም ተጠናቋል። አብዛኛው ሰላም ወዳድ የእምነቱ ተከታዮች በዓሉ በተረጋጋና በሰከነ ሁኔታ እንዲካሄድ ያደረጉት ተሳትፎና ከፀጥታ አካላት ጋር አብሮ ለመስራት ያሳዩት ተነሳሽነት በእጅጉ የሚደነቅና የሚበረታታ ነው፡፡

ታሪካዊ ጠላቶቻችን ኢትዮጵያን ለማተራማስና ለማፍረስ እንደ መሳሪያ ከሚጠቀሙባቸው ጉዳዮች ውስጥ የለውጥ ሂደቱ ፈተና ሆነው የቀጠሉት የሃይማኖት ፅንፈኝነት፣ አክራሪነትና መንደርተኝነት ዋነኞቹ እንደመሆናቸው፤ የውስጥ ባንዳዎች በሃይማኖት ሽፋን ከውጭ ኃይሎችና ከታሪካዊ ጠላቶች ጋር ተቀናጅተው ማህበራዊ ትስስሮቻችንን ለመበጣጠስ፤ በሀገራችን ውስጥ አስተማማኝ ሰላምና መረጋጋት እንዳይሰፍን ለማድረግ እንዲሁም ከአንድነት ይልቅ መበታተንና መከፋፈል እንዲፈጠር አልመው እየሰሩ ይገኛሉ። በተለይም በአማራ ክልል ጎንደር ከተማ ካጋጠመው ረብሻ ጋር ተያይዞ ግጭቱን ወደ ደቡብ ክልል ወራቤ ከተማና ወደ ሌሎች አካባቢዎች በማስፋፋት ሁከትና ብጥብጥ እንዲፈጠር ሙከራ ማድረጋቸው የሚታወስ ነው፡፡

በማህበራዊ ሚዲያዎች ሰሞኑን የፀረ-ኢትዮጵያ አቋሞቻቸውን በመግለፅ ቀጣይ ሊፈጥሩት ስላሰቡት ሁከት በአደባባይ ሲገልፁ ሰንብተዋል። ይህንኑ እኩይ ዓላማቸውን ትናንት በአዲስ አበባ የታላቁ ዒድ ሶላት ላይ ለመተግበር ሙከራ አድርገዋል። በሰማዕታት ሐውልትና በመስቀል አደባባይ በንብረት እና በፀጥታ ኃይሎች ላይ ከደረሰ መለስተኛ ጉዳትውጭ ምንም አይነት ጉዳት ሳይደርስ በሰላም ወዳድ አማኞችና በፀጥታ ኃይሎች ቅንጅት የትርምስ ፍላጎቱና ዕቅዱ ከሽፏል። በመሆኑም መላው ህዝባችን የታሪካዊ ጠላቶቻችን በውስጣችን የሚገኙ የተላላኪዎቻቸውን እኩይ ሴራዎች ተገንዝቦ ፅንፈኝነትንና መገፋፋትን በቁርጠኝነት በመታገል ህብረ ብሄራዊ አንድነቱን ማረጋገጥ አለበት፤ ያሳሰበው መግለጫው፤ መንግሥትም በፅንፈኞች ላይ የሚወስደውን እርምጃም አጠናክሮ እንደሚቀጥል ሲል አረጋግጧል፡፡

ይሄን አይነት የሕዝቦችን አብሮነትና ወንድማማችነት በመሸርሸር እኩይ ፍላጎትን ለማሳካት በጥቂቶች የሚደረግ ጥረት በምንም መልኩ ቢሆን ብዙሃኑን ሊወክል አይችልም። በመሆኑም እኩይ ተልዕኮ ተሸካሚ ጥቂቶች በዝተው እንዲያውኩ እድል መስጠት ስለማይገባም፤ ዘመን የማይሽረውን የህዝቦች አንድነትና መተባበርን በማጎልበት ያለ ልዩነት ሃይማኖትን፣ ብሄርንና መንደርተኝነትን ማእከል ያደረገውን አክራሪነትና ፅንፈኝነትን መዋጋት ይኖርበታል። ይሄን ሲያደርግ እንደ ትናንቱ ሁሉ ዛሬም ሆነ ነገ ፈተናዎቹን በድል መሻገር ይቻላል፡፡

ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**
ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## ለውጡ ከችግር ለምን መላቀቅ ተሳነው?

**ሙሉቀን ታደገ**

ከዓለም ታሪክ እንደተገነዘብነው፤ በአንድ አገር ለውጥ ወይም አዲስ ነገር በመጣ ጊዜ ለውጥ በመጣባት አገር ውስጥ የሚኖሩ ዜጎች በተለያዩ ችግሮች እንደሚፈተኑ ነው። ይሁን እንጂ ከለውጥ ማግስት ለፀብ የጋበዛቸውን ጉዳይ ከስር በመመርመር ለችግሩ ዘላቂ መፍትሄ በመስጠት ወይም በማበጀት አገራቸውን ለትልቅ እድገት ያበቁ በርካቶች መሆናቸውን ታሪክ ያስተምረናል።

በእኛ አገር እንደ አገር ከ1966 ዓ.ም ጀምሮ መሰረታዊ የአገዛዝ ለውጥ የመጣ ቢሆንም ከለውጡ ማግስት የተፈጠሩ ችግሮችን መፍታት አቅቶን ይሄው እስካዛሬ ድረስ በተቸነከርንበት መርዛማ ችንካር እንደተቸነከርን በችግር እየተናጥን እና እርስ በርሳችን እየተበላላን ለአመታት ቀጥለናል። ለዚህም በርካታ አመክንዮች ቢኖሩም ለዛሬው ግን ሁለት አመክንዮችን ለመጥቀስ እሻለሁ።

ከ1966 ዓ.ም ለውጥ ጀምሮ ስለምን ችግራችን መፍታት ተሳነን? ለሚለው አንደኛው ምክንያት የውስጣዊ ሃይሎች የአጀንዳ አመንጭነት ውስንነት መኖር ነው። ማለትም ከለውጥ ማግስት በኢትዮጵያ ለተፈጠሩ ችግሮች ምክንያቶች ወይም አጀንዳዎች ኢትዮጵያን ከሚጠሉ ታሪካዊ ጠላቶች ለኢትዮጵያ ተቀርጸው የተሰጡን እንጂ የህዝባችንን ችግሮች ይፈታሉ ተብለው በመጡ ለውጥ አምጪ ሃይሎች የተቀረጹ ባለመሆናቸው ነው።

ከዚህ ጋር ተያይዞ ለውጡን ያመጡ ሃይሎች በፍላጎታቸውም ይሁን በውጭ ተኩላዎች ተታለው ከታሪካዊ ጠላቶቻችን አጀንዳ በመቀበል ኢንዱአስትሪ በሌለበት አገር ላባደርና ወዛደር በማለት፣ ቢሮ ገብቶ የማያውቅን አርሶ አደር ቢሮክራት በማለት፣ በአንድነቱ ጠንክሮ ቅኝ ገዥዎችን ሳይቀር ያሳፈረን ህዝብ በጎሳው የሚከፋፈል አስተዳደር እና የመንግስት አወቃቀር በመዘርጋት ሲያጋጩን እና ሲያወዛግቡን ኖሩ። ያ ሱሳቸውም አለቃቸው ብሎ ታጥቦ ሊጠሩ የማይችሉ የፖለቲካ ፍልስፍናዎችን በመደረት ዛሬም ድረስ አገር አጥፊ ችግሮችን በገፍ እያመረቱ ይገኛሉ።

ከለውጥ ማግስት ለተከሰቱት ችግሮች መነሻ አጀንዳ የተፈጠረው በውስጥ ሃይሎች ቢሆን ኖሮ ቀኑ ይዘገይ እንደሆነ እንጂ በኢትዮጵያ ሰላም እና እድገት መምጣቱ እንደማይቀር መሆኑን ታሪክ ያስተማረን ሃቅ ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ በአገረ ቻይና የመጣውን ለውጥ እና የፈጀውን ጊዜ ለአብነት ያህል ማየቱ በቂ ነው።

እ.ኤ.አ 1644- 1911 ዓ.ም ቻይና በማንቹ ወይም ቺንግ ሥርዎ- መንግስ ትመራ ነበር። በዚህ አገዛዝ የተማረሩ ኃይሎች በተለይም ደግሞ የቡርዣዋው ክንፍ የሆነው ኬ.ኤም.ቲ እና የኮሚኒስት ክንፍ የነበረው የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ (ሲፒሲ) ቻይናን ለዓመታት ሲገዛት የነበረው ሥርወ መንግስት አሽቀንጥረው ጣሉ። የእነዚህ ሁለት ሃይሎች ትብብር እና ጥምረት የአለምን ህዝብ በአግራሞት እጁን በጉንጩ ላይ ያስጫነ ነበር።

ይሁን እንጂ ቀን ቀንን፤ ዓመትም ዓመትን ሲወልድ ማንቹ ወይም ቺንግ ሥርዎ- መንግስት ለማስወገድ ሳንባችን አጋጥመን በአንድ አንፍንጫ እንተንፍስ ሲሉት የነበሩት ሃይሎች አይን እና ናጫ ሆነው አረፉት። በመካከላቸው የነበረው ቁርቁስ ሰፍቶ እ.ኤ.አ 1926 ዓ.ም የቡርዣዋው ክንፍ የሆነው የኬ.ኤም.ቲ ኃይል የኮሚኒስት ክንፍ የነበረውን የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲን (ሲፒሲ) ለማጥፋት ቆርጦ ተነሳ። በአይነቱ የተለየ ከበባም አደረገ። የኮሚኒስት ክንፍ የነበረው የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲም (ሲፒሲ) ከተደረገበት ከበባ ለመውጣት እና ራሱን ከጥፋት ለመዳን «ሎንግ ማርች» እየተባለ የሚጠራውን 9000 ኪሎ ሜትር የሸፈነ ጉዞ አደረገ። የኮሚኒስት ክንፍ የነበረው የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲም (ሲፒሲ) ከተጋረጠበት ጥፋትም ራሱን አዳነ።

ይህ በእንዲህ እያለ እኤአ 1931 ዓ.ም ጃፓን ቻይናን ወረረች። በዚህም ሁለቱ ለመጠፋፋት የሚፈላለጉ የነበሩ ሃይሎች የውስጥ ጠባቸውን ወደ ጎን ትተው ጃፓንን ለማፋለም በአንድ ላይ ቆሙ። ለአገራቸው ነጻነትም ተዋደቁ። ባደረጉት እልህ አስጨራሽ ትግልም አገራቸውን ከጃፓን ወረራ ነጻ ማድረግ ቻሉ።

ነገር ግን ከነጻነት ማግስት እናት፣ አባት፣ ወንድም.፣ እህት እና ዘመድ የማያውቀው የስልጣን ልክፍት በአገረ ቻይና አገርሽቶ ከአንዴም ሁለቴ አብረው የቆሙትን ኬ.ኤም.ቲ ኃይል እና የኮሚኒስት ክንፍ የነበረው የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲን (ሲፒሲ) ጦር አማዘዘ።

ኬኤምቲ የተሰኘው ክንፍ በኮሚኒስት ክንፍ የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ (ሲፒሲ) ላይ ዳግም ጥቃት ከፈተ። ኬኤምቲም የውጭ ድጋፍ ስለነበረው የኮሚኒስት ክንፍ የነበረው ሲፒሲ (የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ) የሚያሸነፍ መስሎት ነበር። ነገር ግን የኮሚኒስት ክንፍ የነበረው ሲፒሲ(የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ) እውነተኛ ለቻይናውያን እድገት እና ብልጽግና የቆመ ስለነበር ከፍተኛ የህዝብ ድጋፍ ነበረው። በዚህም ኬኤምቲን አሸንፎ ቻይናን አሁን ለደረሰችበት እድገት እንድትበቃ አደረገ። ከጦርነት በኋላ ቻይና እንዴት ለዚህ ልትበቃ ቻለች ? ቢባል መልሱ ከለውጥ ማግስት ለሁለቱ ቡድኖች መነሻ የጸብ አጀንዳ የተፈጠረው በውስጣዊ የቻይና ሃይሎች ስለነበር ነው።

ከ1966 ዓ.ም ጀምሮ በኢትዮጵያ የመጣው ለውጥ ለምን ከችግር መላቀቅ አቃተው ለሚለው ሌላኛው ምክንያት ደግሞ «የሞራል ሴሰኝነት» ወይም «መርህ አልባ አሽቃባጭነት» ነው። ምሁራን በተማሩት ሙያ፤ የበታች ሹሞች ደግሞ የወከላቸውን ህዝብ ፍላጎቶች አቅም በፈቀደው መጠን እንዲያሟሉ ይጠበቃል። ነገር ግን በእኛ አገር «በሞራል ሴሰኝነት» የተጠቁ ምሁሮቻችን እና የበታች ሹሞች የበላይ ጌቶቻቸውን ለማስደሰት ሲሉ መርህ አልባ በሆነ ደረጃ በማሽቃበጥ ሳይማር ያስተማራቸውን ህዝብ በጥቅም እየሸጡ ከኢትዮጵያ ህዝብ ፍላጎት ጋር በተቃርኖ መቆምን እንደ ጀግንነት ሲቆጥሩት ተመልክተናል ! እየተመለከትንም ነው።

ለዚህ ደግሞ ዋና ምክንያቱ የሚከተለው ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ እርሃብን እና ድህነትን ማሸነፍ ዋነኛው ግቡ ሁኖ ሳለ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት እና ተጽኖ ፈጣሪ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ግን የራሳቸውን ጥቅም በማሳደድ እና አገሪቱን በመዝረፍ ይጠመዳሉ። ይህንን ስርቆታቸውን ከህዝብ ለመደበቅ ሲሉ የህዝብን ሰላም ሚያውኩ አጀንዳዎችን ይቀርጻሉ። እነኛ አጀንዳዎች ያድጉና ከቁጥጥር ውጪ ይሆናሉ። በዚህም ሂደት ለውጡ ውሃ ይበላው እና የኢትዮጵያ ህዝብ በችግር እና በስደት ኑሮውን እንዲያሳልፍ ይፈርዱበታል። ህዝብም በዚህ ይቆጣና ከእስክሪፕቶ ነፍጥ ያነሳል። ገዢውንም ያባርራል። ሌላም ቡድን ይተካል። የተተካውም ችግር ይፈታል ሲባል ከበፊቶቹ የተመለከተውን የአስተዳደር አይነት በስም ብቻ ይቀይርና ሁሉም ነገር እንዳለ ያስቀጥለል። መርህ አልባ አሽቃባጮችም በአዲሱ ለውጥ ውስጥ ተጠቃሚነታቸውን ለማስጠበቅ ከዚህ ቀደም ያደርጉት ከነበረው በላይ ማሽቃበጥ ይጀምራሉ። ይህ የማሽቃበጥ አዙሪት ኢትዮጵያን ከችግር እንዳትወጣ ካደረጉ በርካታ ምክንያቶች አንዱ ነው።

በመጨረሻም የለውጥ ሃይሎች ሰላም እና እድገት በማረጋገጥ አገርን ወደፊት የሚያሻግር አጀንዳዎችን በራሳችሁ ቅረጹ፤ ምሁራን እና የበታች ሹሞችም ከሞራል ሴሰኝነት ተላቃችሁ በትክክለኛ መርህ ላይ የተመሰረተ ፖለቲካ አራምዱ መልዕክቴ ነው !!

# ነፃ ሃሳብ

# የኛ ነገር፣... ታጥቦ ጭቃ...!!

**ከአስባቸው ደሳለኝ አበሻ (ለንደን)**

በቅድሚያ ለእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ወገኖቼ፣ እንኳን ለ1ሺህ 443ኛውን የኢድ በዓል በሰላም አደረሳችሁ። ኢድ ሙባረክ ብያለሁ:: እንዴት ሰነበታችሁልኝ ውድ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ አንባቢ ወዳጆቼ:: ሰሞኑን ጎንደር ውስጥ ተፈፀመ የተባለውን ግጭት ካጋጠመው የሰው ሕይወት መጥፋትና የአካል ጉዳት በተጨማሪም በሃይማኖት ተቋማት ላይ ውድመት መድረሱን በማህበራዊ ሚዲያዎችና በሳተላይት ቴሌቪዥኖች ስንከታተል ሰንብተናል። ሃይማኖት በመለኮት ወይም በቅዱስ ሀሳብ ዙሪያ የተቋቋሙ የእምነት፣ የጋራ ምልክት ስርዓት ነው።

ሃይማኖት በህልውና፣ በሞራል እና በመንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ በመርሆዎች፣ በእምነት አሠራሮች ስብስብ የተገነቡ ትምህርቶች ናቸው። ሃይማኖቶች፣ በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ በመኖራቸው የአብሮነት፣ የመከባበር፣ የወንድማማችነት እና የይቅርታ መልዕክቶችን በቋሚነት ያለማቋረጥ የሚያረጋግጡ ናቸው:: ታዲያ፣ የኛ ነገር ከርሞ ጥጃ፣ አድሮ ቃሪያ፣ ታጥቦ ጭቃ....ሆኖብኛል። "ግጭቱ እንዴት ተነሳ? መቼ? የት? እነማን? ለምን አላማ አዘጋጁት?" የሚለውን ጥያቄ ጉዳዩን ለሚከታተሉት የህግ ባለሙያዎች ትቼ፤ ተቀዳሚ ሙፍቲ ሐጂ ዑመር እድሪስ የሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ትኩረት ማድረጉ ጠቃሚ ይመስለኛል።

በመልዕክታቸው፣ ያልተረጋገጠ ወሬ ህዝብን ከህዝብ የሚያጋጭ ጉዳይ መሆኑንም አስገንዝበው፣ ድርጊቱ የትኛውንም ሃይማኖት የማይወክል እንደሆነ አረጋግጠውልናል። በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነትና እውቅና ያላቸውም አካላት ቢሆኑም ግጭት አባባሽ መልእክቶችን በማሰራጨት እልቂት እንዲፈጠር የሚያደርጉትንም ፅንፈኛ ቅስቀሳቸውን እንዲያቆሙ በአባታዊ ተግሳፅ አሳስበዋል:: ህዝቡም የተነገረውን ሁሉ አምኖ መቀበል ብቻ ሳይሆን መርምሮ ማረጋገጥ እንዳለበት የሰጡትን ቁርጥ ያለማሳሰቢያ ሰላም ወዳድ ኢትዮጵያውያንን ሁሉ በደስታ ተቀብለነዋል። አያይዘውም፣ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ኮሚቴ በማቋቋም እና ቦታው ድረስ በማቅናት ችግሩን ለመፍታት ጥረት እንደሚያደርግም ነግረውናል።

ሥልጣኔ ማለት ይህው ነው:: የሠለጠነ ባህል ወይም ኅብረተሰብ የሚገነባው በመነጋገርና በመቻቻል በመተሳሰብ ነው። አንዳንድ ሰዎች ስልጣኔን ሲገልጡት፡- "ስልጣኔ: የፈለጉትን ነገር በፈለጉት ሰዓት ማድረግ መቻል ነው :: ስልጣኔ .... ሁልጊዜ ለውጥ መፈለግ ነው ..... ስልጣኔ፡ ንጹህ መሆንና በንጹህ አካባቢ መኖር ነው....... ስልጣኔ፡ ሌላውን ያለመረበሽ እና ራስም ያለመረበሽ ፍላጎት ያለው መቻቻል መተሳሰብ መረዳዳት... የሰውን ሁሉ መብት ለማክበር የመፈለግ እሳቤ ነው:: ...... ስልጣኔ: ለችግር ሁሉ መፍትሄ ለማምጣት የሚያስችል መተባበር ነው፤" ብለው ያምናሉ። እኔም በዚህ ሐሳብ እስማማለሁ።

በእርግጥ ሃይማኖት ለአንድ ኅብረተሰብ የሚያምንባቸው ጽኑ መሰረት እምነቶች በመሆናቸው በዓለም ውስጥ በርካታ ልዩ ልዩ ሃይማኖቶች ተፈጥረው ዛሬ በሚሊዮን የሚቆጠር ተከታዮች አፍርተው ዓለም በመቻቻል ነው የሚኖረው። ከነዚህም ሃይማናቶች ዋና ዋናዎቹ በይፋ የመንግሥት ሃይማኖት በመባል ተቀባይነት ካገኙት ውስጥ ክርስትና፣ እስልምና፣ አይሁድና፣ የሕንዱ ሃይማኖት እና ቡዲዝም ዓለም አቀፋዊ እውቅና ተሰጥቷቸዋል:: ከነዚህ ታላላቅ ሃይማኖቶች ውስጥ አንዱ የሆነው እስልምና ነው:: እንደዚህ እንደዛሬው ከዓለም ጫፍ እስከ ዓለም ጫፍ እንዲስፋፋና ብዙ ተከታዮች አግኝቶ እንዲበለፅግ ኢትዮጵያ ቀዳሚውን ድርሻ ትይዛለች።

> **በማህበረሰባችን ውስጥ እንዲህ አይነት ሃይማኖታዊ ስነ ምግባር የሚያስተካክል መሪ ከሌለ ወግና ስርዓት አይኖረንም። እረብሻው፣ ግድያው፣ ብጥብጡ፣ ስርዓት አልበኝነቱ ይቀጥላል። ሕግና ስርዓት ከሌለ ደግሞ ነውር ወይም ክብር አይኖርም :: ሥነ-ምግባር ደግሞ በማህበረሰብ ውስጥ ተቀባይነት ያለውንና የሌለውን ድርጊት መለየትና ነውር የሆነውን ድርጊት ነቅሶ በማውጣት ወይንም በማስወገድ እንደ ተቀዳሚ ሙፍቲህ ክቡር ዶክተር ሀጂ ሑመር ኢድሪስን የሚመስሉ ጠንካራ የሃይማኖት አባቶች ከሌሉ ከዚህ የባሱ ብዙ ማህበራዊ ቀውሶች ወደፊት መምጣቸው አይቀሬ ነው**

ምክንያቱም የነብዩ መሐመድ ተከታዮች ስለ እስልምና ሃይማኖታቸው በመካ እንግልት ሲደርስባቸው ተከታዮቻቸውን የላኩት ወደ ኢትዮጵያ ነው። ይህ ባይሆን ኖሮ ምን ሊሆንና ሊፈጠር እንደሚችል አይታወቅም። እናም እነዚያ የነብዩ መሃመድ ተከታዮች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ራሳቸውን በማዳናቸውና በኢትዮጵያ በመጠለላቸው፤ ኢትዮጵያ ለእስልምና ሕልውናም መስፋፋትም ከፍ ያለ ሚና እንዲኖራት ሆኗል። ይሄን የምለውም ያለምክንያት አይደለም። ይልቁንም የሆነውንና የተፈጸመውን በማስረጃነት በመያዝ ነው። እንዴት ቢሉ በወቅቱ የእስላም አህዳዊ ጥሪ ፈጽሞ መስማት ያልፈለጉት የመካ ቁረይሾች በሙስሊሞች ላይ የቅጣት በትራቸውን አሳረፉ። አማኞቹ በደረሰባቸው ግፍ እና መከራን በመመረር በገዛ ወገኖቻቸው እየተገደሉ ከእምነታቸው በመመለስ እንደነርሱ የጣኦት አምልኮት ይከተሉ ዘንድ ማእቀብ፣ እየተጣለባቸው ስቃይ እና ሞት ግፍና ብስቁልና ተፈፀመባቸው።

በዚህን ጊዜ ነብዩ ሙሀመድ በ610 እ.ኤ.አ. የነብይነት ማእረግ አግኝተው ስለነበር በመካ ወደ ኢስላም ጥሪ በማድረግ ባልደረቦቻቸው ላይ የሚፈጸመውን ጥቃት ሊከላከሉ እንደማይችሉ ሲገነዘቡ ፤ "ፊጣሪአቸውን በነጻነት ማምለክ የምትችሉት ወደ ሀበሻ ሐገር ስትሰደዱ ነው" በማለት ነብዩ ሙሀመድ ተከታዮቻቸውን በመምከራቸው ወደ ኢትዮጵያ የላኳቸው መሆኑን የተለያዩ ድርሳናት ያመለክታሉ። በወቅቱ ነብዩም በግፍና በመከራ ያሉትን ተከታዮቻቸው እንደዚህም አልዋቸው። " ወደ ሀበሻ ሐገር ተሰደዱ በርስዋ አንድ ንጉስ አለ ። ከርሱ ፊት ማንም ተበዳይ አይሆንም ፤ "አላህ ካላችሁበት ሁኔታ አውጥቶ ድል እስክትጎናጸፉ ድረስ...." ሒዱ በማለት አሰናበቷቸው።

ታሪክ እንደሚያረጋግጥልን ግንኙነቱ የተጀመረው ኢስላም ከየትኛውም አገር ከመድረሱ አስቀድሞ በፊት ከቅድስቲትዋ መካ ከተማ በመነሳት ወደ ሐበሾች ሐገር ኢትዮጵያ ነው የደረሰው :: በዚህም መሰረት ከነብዩ ሙሀመድ ትእዛዝ ተቀብለው የመጀመሪያውን ስደት (ሂጅራ) ወደ ሀበሻ ወደ ቅድስት ሐገር ኢትዮጵያ የደረሱት አሥራ ሁለት ሁነው ነበር ። ከስደተኞቹ መካከል የነብዩ ሙሀመድ ሴት ልጅ ሩቅያ ቢንት ሙሀመድ እና ባለቤትዋ (በኋላ ሳይሶስተኛ ኸሊፋ ወይንም የሳዑዲ ንጉስ የሆኑት)። ኡስማን ቢን አፋን ይገኙበት ነበር ። በማለት አያሌ የታሪክ ድርሳናት ስናገላብጥ የሚሰጠን ምስክርነት ይህንኑ ሐቅ ነው ::

የሃይማኖት ነፃነት እና የሃይማኖት እኩልነት በማረጋገጥ ኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ ታሪክ አለት። ይሄን በተመለከተም ከተለያዩ ሰነዶች ማመሳከር፤ ከታሪክም ብዙ ነገሮችን መማር እንችላለን። ታሪክ የማንኛውም ሀገር ንብረት ነው ። ማንኛውም የአገሩ ዜጋ የእምነት ታሪኩን ጠንቅቆ ማወቅ አለበት ። በዚህ ውስጥ ፣ ያለጥርጥር ፣ መምህራንና የሃይማኖት አባቶች፣ የሚዲያ ተቋማት ትክክለኛውን ትምህርት በመስጠት ትውልዱን ማዳን ይኖርባቸዋል ::

በሰው ልጆች የስነልቦናዊ አመለካከት ቢሆንም የፍቅርና የጥላቻ ስሜት ገብቶት በአዕምሮው ብስለት ካልበለፀገ በቀር የህብረተሰብ ተቆርቋሪነትና ሃይማኖታዊ እምነትን ብቃት ባለው ኃላፊነት ለመምራት እጅግ ይከብዳል:: ጊዜው ቆየት ቢልም፣ ተቀዳሚ ሙፍቲ ሐጂ ዑመር እድሪስ፣ በአንድ ወቅት ንግግር ሲያደርጉ ያዳመጥኩት ቁምነገር አለ: : " በዘረኝነት ተከፋፍለናል:: ደም አፍስሰናል! :: ደሀው የሚልብሰው አቶ የሚጠለልበት ፈርሶ ! በባለ ጠጋው እየተበደለ ፍርድ ሲጓደል እኛም የሃይማኖት አባቶች መገሰፅ ፣ መምከር፣ ማስተማር ፣ መመለስ ሳንችል ፣ ምህረት መጠየቅ ዋጋ የለውም !! ። ፈጣሪ ከዚህ የከፋ ቅጣት ያሰበ ይመስለኛል !! ። እኛ ከመናገር ባለፈ በተግባር ፣ ከክፉ ሥራችን ተመልሰን ፀሎት (ዱአ) ብናደርግ ምህረት የማናገኝበት ምክያት ያለ አይመስለኝም።" በማለት ኀዘንና ቁጭት በተቀላቀለበት ስሜት በጋራ በተዘጋጀው የፆሎት ሥነሥርዓት ላይ ለመንግሥት ባለስልጣኖችና ለክርስትና እምነት አባቶች ያስተላለፏትን መልዕክት ምንጊዜም አረሳትም።

ይሄን ንግግራቸውንና መልዕክታቸውን ባሰብኩ ቁጥር እንዲህ አይነት ሲናፍቀን የኖረ ትክክለኛ ሃይማኖታዊ አባት አሁንም ወደፊትም በእጅጉ እንደሚያስፈልገን አስባለሁ:: በማህበረሰባችን ውስጥ እንዲህ አይነት ሃይማኖታዊ ስነ ምግባር የሚያስተካክል መሪ ከሌለ ወግና ስርዓት አይኖረንም። እረብሻው፣ ግድያው፣ ብጥብጡ፣ ስርዓት አልበኝነቱ ይቀጥላል። ሕግና ስርዓት ከሌለ ደግሞ ነውር ወይም ክብር አይኖርም:: ሥነ-ምግባር ደግሞ በማህበረሰብ ውስጥ ተቀባይነት ያለውንና የሌለውን ድርጊት መለየትና ነውር የሆነውን ድርጊት ነቅሶ በማውጣት ወይንም በማስወገድ እንደ ተቀዳሚ ሙፍቲህ ክቡር ዶክተር ሀጂ ኡመር ኢድሪስን የሚመስሉ ጠንካራ የሃይማኖት አባቶች ከሌሉ ከዚህ የባሱ ብዙ ማህበራዊ ቀውሶች ወደፊት መምጣቸው አይቀሬ ነው ::

በእርግጥ በሰዎች መካከል ብዙ ልዩነቶች አሉ :: ልዩነት ወይም መለያየት ማለት አንድ ሰው በሃይማኖቱ፣ በቋንቋው፣ በብሔሩ፣ በቀለሙ፣ በአመለካከትና በንግግር በሀሳብ ከሌላው ሰው የተለየ ሊሆን ይችላል :: ነገር ግን የሚያስማሙን ጉዳዮች ላይ ተባብረን ሀገራችንን መገንባት ይኖርብናል :: በተለያየንባቸው ጉዳዮች ላይ ደግሞ አንደኛችን ለአንደኛችን ሆደ ሰፊ ሆነን በሰለጠነ መልክ ችግሮቻችንን እንደ ሀገር ተመካክረን መፍታት ተገቢ ነው :: የተለያዩ ሃይማኖቶች በመከተላችን ብቻ ኢትዮጵያዊነታችንን የሚቀይር ምድራዊ ኃይል በፍፁም ሊኖር አይገባውም።

ይህ እውነት እንደተጠበቀ ሆኖ ግን ከልዩነት አቀንቃኝነት ይልቅ አንድነት፣ ሕብረትና ወንድማማችነትን፣ ከመገፋፋትና ፀብ ይልቅ መተባበር፣ መረዳዳትና በፍቅር አብሮ መኖርን፤ ከጥላቻና በቀል ይልቅ መተሳሰብና ይቅር ባይነትን ለትውልዱም፤ ለምዕመኑም ማሳወቅ የተገባ መሆኑ ሊዘነጋ አያስፈልግም። ለዚህ ደግሞ ከሃይማኖታዊና ፍልስፍና ስነ ምግባር ጋር በተያያዘ ጉዳዮች ወላጆች ልጆቻችሁን የሃይማኖት አባቶች ተከታዮቻችሁን መምህራኖች ተማሪዎቻችሁን ፣ በስነ ምግባር የታነፁ እንዲሆኑ ቀዳሚ ኃላፊነት መውሰድ እንዳለባችሁ ተገንዝባችሁ ገና ብዙ ብዙ ሥራ ይጠብቅናል!!

ይሄን ኃላፊነታችንን በየዘርፉ፣ በየ ሙያ ተቋማቱ፣ በየእምነት ተቋማቱ፣ ወዘተ. በሚገባ ያለመወጣታችን ውጤት ነው ዛሬ ላይ ታረቁ በተባለ ማግስት መጣላት፣ ተስማሙ በተባለ ማግስት መለያየት፣ ሰላም ወረደ በተባለ ማግስት ጦር መማዘዙ፣ ስለ እምነታቸው የተሻለን ሸተው በአንድ ቆሙ ባልን ማግስት ድንጋይ መወራወሩና ንብረት ማውደሙ፣... እየተፈራረቀብን፤ የኛ ነገር "ከርሞ ጥጃ፣ አድሮ ቃሪያ፣ ታጥቦ ጭቃ...." ይሉት እየገጠመን ያለው። ይህ ደግሞ መሆን ስለሌለበት ሁሉም በየተሰማራበት ሁሉ ለአብሮነት፣ ለመቻቻልና ወንድማማችነት፣ ለፍቅርና አንድነት፣ ለእኩልነትና ፍትህ ቅድሚያ ሰጥቶ በትምህርቱም፣ በስብከቱም ትውልዱን ሊያስገነዝብና ሊያንጽ ይገባል።

በዚህ ረገድ የታላቁን የረመዳን ወር መጠናቀቅ ተከትሎ ትናንት በአዲስ አበባ በነበረው የኢድ ሶላት ወቅት የሆነውን ማንሳቱ ተገቢ ነው። ምክንያቱም ታላቁን የኢድ ስግደት ገጽታ ለማጠልሸት በጥቂት አካላት ተደረገ የተባለው ከሃይማኖቱ ያፈነገጠ ተግባር ሊደገም ስለማይገባው ብቻ ሳይሆን፤ ትልቁን እውነት በጥቂት አጀንዳ ተሸካሚ ግለሰቦች ተግባር ሊሸፈን ስለማይገባው ነው። ትናንት በኢድ ሰላት ወቅት ሆነ ተብሎ በማህበራዊ ሚዲያ በቀጥታ በተሰራጩ ቪዲዮዎች እንደታዘብነው፤ በዓሉ በደመቀ ሁኔታ እንዳይከበርና የሶላት ስነ-ስርዓቱን ለማወክ በሚመስል መልኩ ምክንያቱ በማይታወቅ ሁኔታ ግለሰቦች ባስነሱት ብጥብጥ እንደ ጎንደሩ እና ሌሎችም ቦታዎች እንደሆኑት ሁሉ በአዲስ አበባ ከተማ ለመድገም መታሰቡ እጅጉን የሚያሳዝን ድርጊት ነው።

ምንም እንኳን በዚህ የጥቂቶች አስነዋሪድርጊት የትልቁ በዓል ታላቅ ድምቀት የማይደበዝዝ ቢሆንም፤ ተግባሩ የኖረውን አብሮነት፣ እስላማዊ የሰላም ባለቤትነትና እሴት ለማጉደፍ፣ ከሰላም ይልቅ ከረብሽ አትራፊ የሆኑ ኃይሎች ሀሳብ እንዲሳካ ታልሞ የተፈጸመ እንደመሆኑ ሊወገዝ ይገባዋል። በተለይ መላው ሙስሊም ባጠቃላይም ሕብረተሰቡ በጋራ ሊያወግዘው የሚገባ ነው። ታላላቅ መልካም ገጾችን ለማጠልሸትና መሰል የጥፋት አጀንዳን አንግበው ለጥፋት የሚሰማሩ ቡድኖችና ግለሰቦችን መንግሥትም ኮስተር በማለት ጠንካራ እርምጃ መውሰድ ግዴታውን ሊወጣ ያስፈልጋል። ምክንያቱም በእነዚህ አይነት እኩያን ምክንያት የሚገለጸው አገር ነው፤ ሃይማኖት ነው፤ ሕዝብ ነው፤ ማንነት ነው፤...። ይህ ሲሆን ደግሞ "ከርሞ ጥጃነት፣ አድሮ ቃሪያነት፤ ታጥቦም ጭቃነት የሚሰጠው ለእኩያኖቹ ግብር ሳይሆን፤ በደምሳሳው ለሰፊው አገርና ሕዝብ መሆኑን ልንገነዘብ ያስፈልጋል። ይህ ደግሞ እንደ ሰለጠነ ሕብረተሰብ ብሔራዊ ውርደት ነው። ይህ እንዳይሆን ልቦና ይስጠን፤ እያልኩ፤ ለዛሬው በዚሁ አበቃሁ፤ በሌላ ጽሑፍ እስክንገናኝ ቸር ይግጠመን!

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## እየተራቀቀ የመጣው የሮኬት ሳይንስና የአገራችን ፋና ወጊው የሮኬት ማስወንጨፍ

**መሳኩ ኤሮሴ**

ከሮማዊያን ዘመን ጀምሮ ለብዙ ሺህ ዓመታት ለሮኬት ሳይንስ መሰረት የሆኑ ምርምሮችና ሙከራዎች ሲደረግ ቢቆይም ለዘመናዊ ሮኬት ሳይንስ መሰረት የተጣለው በ17ኛው ክፍለ ዘመን እንደሆነ ድርሳናት ያስረዳሉ። በ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መገባደጃ ላይ ለዘመናዊ ሮኬቶች ሳይንሳዊ መሰረት የተጣለው በታላቁ እንግሊዛዊ ሳይንቲስት ሰር አይዛክ ኒውተን (1642-1727) ነው። ኒውተን ስለ አካላዊ እንቅስቃሴ ያለውን ግንዛቤ በሦስት ሳይንሳዊ ሕጎች አደራጅቷል። ሕጎቹ ሮኬቶች እንዴት እንደሚሠሩ እና ለምን በውጫዊ ክፍተት ውስጥ መሥራት እንደሚችሉ ያብራራሉ።

የኒውተን ህጎች ብዙም ሳይቆይ በሮኬቶች ዲዛይን ላይ ተግባራዊ ተጽእኖ ማሳደር ጀመሩ። በ1720 አካባቢ አንድ ሆላንዳዊ ፕሮፌሰር ቪለም ግራቬሳንዴ በእንፋሎት አውሮፕላኖች የሚንቀሳቀሱ ሞዴል መኪናዎችን ሠሩ። በጀርመን እና ሩሲያ ውስጥ የነበሩ የሮኬት ሞካሪዎች ከ45 ኪሎ ግራም በላይ ክብደት ያላቸው ሮኬቶችን መስራት ጀመሩ። ከእነዚህ ሮኬቶች መካከል አንዳንዶቹ በጣም ኃይለኛ ከመሆናቸው የተነሳ ሮኬቶቹ ገና ከመነሳታቸው በፊት በጭስ ማውጫው የሚንበለበሉ ነበልባሎች በመሬት ውስጥ ጥልቅ ጉድጓዶችን የሚቆፍሩ ነበሩ።

በ18 ኛው ክፍለ ዘመን መገባደጃ እና በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ሮኬቶች እንደ የጦር መሳሪያ ደግም ጥቅም ላይ መዋል ጀመሩ:: እ.ኤ.አ. በ 1792 እና በ 1799 በብሪታንያ ላይ የተተኮሰው የህንድ ሮኬቶች ስኬታማ መሆናቸው የመድፍ ኤክስፐርቶች ፍላጎት መሳብ ቻለ። በተለይም የእንግሊዛዊውን የመድፍ ኤክስፐርት ኮሎኔል ዊልያም ኮንግሬቭን ፍላጎት ሳበ። ኮንግሬቭ ለብሪቲሽ ወታደሮች የሚውል ሮኬቶችን ለመንደፍ ተነሳ።

የኮንግሬቭ ሮኬቶች በውጊያው ከፍተኛ ስኬት ነበራቸው። በዘመኑ የነበሩ ሮኬቶች በተለይም በከበባ ጊዜ በሺዎች የሚቆጠሩ ሮኬቶች በጠላት ላይ በመተኮስ ከበባውን ለመስበር ጥቅም ላይ ይውል ነበር። . ከዚያን ወቅት ጀምሮ በመላው ዓለም የሮኬት ተመራማሪዎች የሮኬቶችን ትክክለኛነትን ለማሻሻል ጥረት አድርገዋል። እንግሊዛዊ ዊልያም ሄል የሮኬቶችን እንቅስቃሴ መቆጣጠሪያ ዘዴ ፈጥሮ ነበር።

ሮኬቶች ከዚያ በኋላ በመላው አውሮፓ አህጉር በሚደረጉ ጦርነቶች በተሳካ ሁኔታ መጠቀማቸውን ቀጥለውም ነበር። ነገር ግን ብዙም ሳይቆይ ሮኬቶች ለጦርነት ብቻ ሳይሆን ለሰላማዊ ተግባራትም ጥቅም ላይ እንዲውሉ ተደርገዋል። እ.ኤ.አ. በ 1898 አንድ የሩሲያ ትምህርት ቤት መምህር የነበረው ኮንስታንቲን ፂዮልኮቭስኪ (1857-1935) በሮኬት የጠፈር አሰሳ ሀሳብ አቀረበ። ሮኬቶችን ለጠፈር አሰሳ ጥቅም ላይ ለማዋል የሚረዱ የተለያዩ ሀሳቦችንም ማቅረብ ችሎ ነበር። ፂልኮቩስኪ ለዘርፉ ትልቅ አስተዋጽኦ በማበርከቱ የዘመናዊ የጠፈር ምርምር አባት ተብሎ እስከመጠራት ደርሷል።

የሮኬት ሳይንስን ወደ ተሻለ ደረጃ ለማድረስ የሚደረገው ጥረት በ20ኛው ክፍለ ዘመንም ተጠናክሮ ቀጥሎ እንደነበር ናሳ ባሳተመው መጣጥፍ ላይ አመላክቷል። በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ አሜሪካዊው ሮበርት ኤች ጎዳርድ (1882-1945) ተግባራዊ ሙከራዎችን አድርጓል። ችግሮች ቢያጋጥሙትም ጎድዳርድ የመጀመሪያውን የተሳካ በረራ መጋቢት 16 ቀን 1926 አሳካ። በፈሳሽ ኦክሲጅንና ቤንዚን ተጭኖ ሮኬቱ ለሁለት ሰከንድ ተኩል ብቻ በመብረር 12.5 ሜትር ከፍታ በመውጣት 56 ሜትር ርቀት ላይ አረፈ። በዛሬው መመዘኛዎች፣ በረራው አስደናቂ አልነበረም፣ ነገር ግን በ1903 በራይት ወንድሞች እንዳከናወኑት እንደ መጀመሪያው የአውሮፕላን በረራ፣ የጎድዳርድ ቤንዚን ሮኬት በረራ የዘመኑ ፈር ቀዳጅ ስራ ነበር።

ሦስተኛው ታላቅ የጠፈር አቅኚ ኸርማን አበርት (1894-1989) በ1923 ስለ ሮኬት ወደ ጠፈር ጉዞ መጽሐፍ አሳተሞም ነበር። የእሱ ጽሑፎች ለዘርፉ እድገት እጅግ ጠቃሚ ነበሩ። በጽሁፎቹ ምክንያት በአለም ዙሪያ ብዙ የሮኬት ዘርፍ ተመራማሪዎች ተፈጥረዋል። በጀርመን ውስጥ የዚህ አይነት ማህበረሰብ ምስረታ የሆነው ቬሬይን ፋር ራምሺፋህርት (ማህበረሰብ ለስፔስ ቱሪስት) የ V-2 ሮኬት እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል። ይህም በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ለንደን ላይ ጥቅም ላይ ውሏል። እ.ኤ.አ. በ 1937 የጀርመን መሐንዲሶች እና ሳይንቲስቶች ኦበርትን ጨምሮ በባልቲክ ባህር ዳርቻ ላይ በፔኔሙንድ ተሰበሰቡ። በዚያ በጊዜው እጅግ የላቀ ሮኬት በቨርንሄር ቮን ብራውን ዳይሬክተርነት ተገንብቶ ይበር ነበር።

ቪ-2 ሮኬት (በጀርመን A-4 ተብሎ የሚጠራው) ከዛሬዎቹ ሮኬቶች ጋር ሲነጻጸር ትንሽ ነበር። በየሰባት ሰከንድ አንድ ቶን በሚደርስ ፍጥነት የፈሳሽ ኦክሲጅን እና የአልኮሆል ቅልቅል የሚፈጅ ነው። አንዴ ከተከፈተ ቪ-2 መላውን የከተማ ብሎኮች ሊያወድም የሚችል አስፈሪ መሳሪያ ነበር።

እንደ እድል ሆኖ በወቅቱ አላይድ ፎርስ ተብሎ ይጠሩ የነበሩት እንግሊዝና አጋሮቹ V-2 ሮኬቶችን መጠቀም አልጀመሩም ነበር። ይህንን መሳሪያ መጠቀም የጀመሩት በጦርነቱ ማብቂያ ላይ ነው። በጦርነቱ ማብቂያ የጀርመን የሮኬት ሳይንቲስቶች እና መሐንዲሶች አትላንቲክ ውቅያኖስን በመሻገር ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ሊያርፉ የሚችሉ የተራቀቁ ሚሳኤሎች ዕቅድ አውጥተውም ነበር።

በጦርነቱ ጀርመን መሸነፏን ብሎም ለውድቀት መዳረጓን ተከትሎ፣ ብዙ ጥቅም ላይ ያልዋሉ V-2 ሮኬቶች እና አካላት በእነ እንግሊዝ በሚመራው አላይድ ሀይል እጅ ውስጥ ገብተዋል። ብዙ የጀርመን ሮኬት ሳይንቲስቶች ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ተሸገሩ። ሌሎች ደግሞ ወደ ሶቪየት ህብረት ሄዱ።

ዩናይትድ ስቴትስም ሆነች የሶቪየት ኅብረት የሮኬቶችን አቅም እንደ ወታደራዊ መሣሪያ ተገንዝበው የተለያዩ የሙከራ ፕሮግራሞችን ጀመሩ። መጀመሪያ ላይ ዩናይትድ ስቴትስ ከጎድደርድ ቀደምት ሃሳቦች ውስጥ አንዱ በሆነው ከፍታ በከባቢ አየር የሚነፋ ሮኬቶችን የያዘ ፕሮግራም ጀመረች። በኋላም የተለያዩ መካከለኛ እና ረጅም ርቀት አቋራጭ ሚሳኤሎች ተሰራ። እነዚህ የአሜሪካ የጠፈር ፕሮግራም መነሻ ሆኑ። እንደ ሬድስቶን፣ አትላስ እና ታይታን ያሉ ሚሳኤሎች በመጨረሻ ጠፈርተኞችን ወደ ህዋ ማጓጓዣ ሆኑ።

እ.ኤ.አ ኦክቶበር 4, 1957 በሶቭየት ኅብረት ምድርን የምትዞር ሰው ሰራሽ ሳተላይት በማምጠቅ ዓለምን አስደነቀች። ስፑትኒክ 1 እየተባለ የሚጠራው ሳተላይቱ በሁለቱ ልዕለ ኃያላን አገራት መካከል በተደረገው የኅዋ ውድድር ያስጀመረች የመጀመሪያዋ የተሳከ ሮኬት ነበረች። አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሶቪየቶች ላይካ የተባለ ውሻ የያዘች ሳተላይት ወደ ህዋ አመጠቁ። እሽቅድድሙ አልቆመም። ከጥቂት ወራት በኋላ አሜሪካኖች ሌላ ሮኬት አመጠቁ። ሮኬቱ የአሜሪካ መከላከያ ሀይል ነበር። በ1958 አሜሪካኖች የህዋ ፕሮግራም (ናሳን አቋቋሙ)። ናሳ ከወታደራዊ እሽቅድድም ይልቅ ለሰላማዊ ዓላማ ህዋና ማሰሻ ሆኖ ቀጠለ።

ናሳ ከተቋቋመ በኋላ በርካታ ሰዎች እና ማሽኖች ወደ ህዋ መጥቀዋል። የህዋ ተመራማሪዎች በጨረቃ ላይ እንዲያርፉ ተደርገዋል። ሮቦቶች ወደ ተለያዩ ፕላኔቶች ተጉዘዋል። ህዋ ለምርምርና ለንግድ ክፍት ሆኗል። ሳተላይቶች ሳይንቲስቶች ዓለማችንን እንዲያጠኑ፣ የአየር ሁኔታን እንዲተነብዩና በዓለም ዙሪያ ፈጣን ተግባቦት እንዲኖር አስችለዋል። ሳይንቲስቶች ዓለማችንን የበለጠ የመፈተሽ ፍላጎት እየጨመረ በመሆኑ አሁን ካሉት የበለጡ ሮኬቶችን መገንባት አስፈላጊ እየሆነ ነው። የሮኬት ቴክኖሎጂ ከተጀመረበት ከብዙ ሺህ ዓመታት ወዲህ የሮኬት ቴክኖሎጂ ከአነስተኛ ተተኳሽ ቴክኖሎጂ ወደ ስፔስ ትላልቅ ማሽኖችን ይዞ መንቀሳቀስ የሚችል ሆኗል። ሮኬቶች ዩኒቨርስን ለሰው ልጅ ክፍት አድርገዋል።

**የአገራችን ፋና ወጊው ሮኬት የማስወንጨፍ ዜና**




የሮኬት ሳይንስ በዓለም ላይ ብዙ ዘመናትን ያስቆጠረና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተራቀቀ የመጣ ዘርፍ ቢሆን በኢትዮጵያ ግን እንደ ቅንጦት ይታያል። ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ ከሚደረግ መጠነኛ እንቅስቃሴ ውጪ ይህ ነው የሚባል ስራ አልተሰራበትም። ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ ኢትዮጵያ ለተለያዩ ዓላማዎች የሚውሉ ሮኬቶችን የማስወንጨፍ ሙከራዎች እየተደረጉ ነው። አምና በባህር ዳር ከተማ የሚኖሩ ታዳጊዎች በተሳካ ሁኔታ ሮኬት ማስወንጨፋቸውን የመገናኛ ብዙሃን ዘግበዋል። እነዚህ ታዳጊዎች ያደረጉት የተሳከ ሙከራ በብዙዎች ዘንድ ግርምትን የፈጠረ ነበር። በቅርቡ ደግሞ የደብረታቦር ዩኒቨርሲቲ በአጼ ቴዎድሮስ ስም የተሰየመ ሮኬት የማስወንጨፍ ሙከራ ማድረጉን በቅርቡ ይፋ አድርጓል። የማስወንጨፍ ሙከራውም የተሳከ እንደነበር ተዘግቧል። ይህን የአጼ ቴዎድሮስን 154ኛ የሰማዕትነት በዓል ምክንያት በማድረግ የተከናወነ ነው። በመጠን አነስ ያለ ሮኬት ደግሞ በልዑል ዓለማየሁ ስም መወንጨፉን ነው የተጠቆመው።

የዩኒቨርሲቲው ተግባር ለብዙዎች ኩራት እንድሰማቸው ያደረገ ነው። አገሬ በሮኬት ቴክኖሎጂ ወደፊት ከሌሎች ያደጉት አገራት ተርታ ልትሰለፍ ነው የሚል ተስፋ እንዲሰንቅ አድርጓል። በቀጣይ በህዋ በሚደረገው እሽቅድድም ውስጥ አንዷ እንድትሆንም መሰረት የሚጥል ተደርጎ ተወስዷል። ኢትዮጵያ በቴክኖሎጂው ዘርፍ በአጭር ጊዜ ውስጥ አለም የደረሰችበት ቦታ ለመድረስ ዳዴ ማለቷ ይበል የሚያሰኝ ነው። የደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ ተግባር ኢትዮጵያዊያን ኩራት እንዲሰማቸው ያደረገ ነው። አገሬ በሮኬት ቴክኖሎጂ ወደፊት ከሌሎች ያደጉት አገራት ተርታ ልትሰለፍ ነው የሚል ተስፋ እንዲሰንቅ አድርጓል። በቀጣይ በህዋ በሚደረገው እሽቅድድም ውስጥ አንዷ እንድትሆንም መሰረት የሚጥል ተደርጎ ተወስዷል።

የዩኒቨርሲቲው የኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ዳዊት ብርሃኑ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደተናገሩት፤ የዩኒቨርሲቲው የሮኬት ሳይንስ ማዕከል ጥናትና ምርምር አድርጎ ሮኬት የማስወንጨፍ ጥረት ሲያደርግ የዘንድሮው ለሁለተኛ ጊዜ ነው። የዛሬ ዓመት ሙከራ አድርጎ ነበር። አምና በተለምዷዊ መንገድ ለማስወንጨፍ ጥረት አድርጓል። የአምናው ሙከራውም የተሳከ ነበር። የአምናው ወደ 1 ነጥብ 5 ኪሎ ሜትር ማስወንጨፍ የተቻለ ሲሆን በበይነ መረብ የታገዘ አልነበረም። በወቅቱ አገሪቱ ጦርነት ውስጥ ስለነበረች ስለሮኬቱ ማስወንጨፍ ብዙም አልተወራለትም። በብዙ ሰዎች ዘንድም አልታወቀም። በቦታው በነበሩ ሰዎች ግን መገረምን የፈጠረ ነበር።

እንደ አቶ ዳዊት ማብራሪያ፤ ዩኒቨርሲቲው እስከ 5 ኪሎ ሜትር መጓዝ የሚችል የተሳከ የሮኬት ማስወንጨፍ ሙከራ አድርጓል። ከአምናው የተሻለ ሁኔታ ስላለ ቦታ ተመርጦ፤ የደቡብ ጎንደር ዞን የጸጥታ ዘርፍ ኃላፊዎች፣ የሚዲያ አካላት እና የተለያዩ ተጋባዥ እንግዶች ባሉበት አሞራ ገደል የተሳከ የማስወንጨፍ ሙከራ ተደርጓል።

ዩኒቨርሲቲው ዘንድሮ ያደረገውን የተሳከ ሙከራ የዛሬ ዓመት ካደረገው ለየት የሚያደርገው የሮኬት ማስወንጨፍ ስርዓቱን ከበይነ መረብ ጋር የተገናኘ መሆኑ ነው። ይህንም በሁለት በኩል የሚታይ ነው። በአንድ በኩል ዩኒቨርሲቲው በአፍሪካ የመጀመሪያው ኢንዱስትሪ ተጸንሶ የተወለደበት የጋፋት ኢንዱስትሪ አቅራቢያ የሚገኝ ዩኒቨርሲቲ እንደመሆኑ የአጼ ቴዎድሮስን የቴክኖሎጂ ጥማት ለመመለስ አንድ እርምጃ ወደ ፊት መሄዱን የሚያመላክት ነው።

ሌላኛው እንደ አገር ኢትዮጵያን የቴክኖሎጂ አካሄድ ውስጥ ግንባር ቀደም እንድትሆን የሚያስችሉ አገር በቀል ልሂቃን መኖራቸውን የሚያመላክት ነው። ይህ ለአገሪቱ የሮኬት ቴክኖሎጂ ዘርፍ ትልቅ ተስፋ የሚሰጥ ነው። እንደ ኢትዮጵያ በከፍተኛ ትምህርት ደረጃ የሮኬት ሳይንስ በንድፈ ሀሳብ ደረጃ ብቻ ሳይሆን በተግባር መገለጥ መጀመራቸው በተለይም በደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ የሚደረገው የሮኬት ሳይንስ እንቅስቃሴ የኢትዮጵያ የወደፊት መጻኢ እድሏ የተሻለ እንዲሆን የሚረዳ ነው። የአገሪቱን የሮኬት ሳይንስ አቅምና የሮኬት ሳይንስ ጥበብ የተሻለ ደረጃ ላይ ማድረስ እንደሚቻል አመላካች ነው ብለዋል።

ወደፊት ይፋ የሚሆኑ በርካታ ስራዎች አሉ። ዩኒቨርሲቲው ከሮቦቲክስ ጋር የተገናኙ ሌሎች ስራዎችንም እየሰራ ነው። ከሬዲዮ ጋር የተገናኙ ስራዎችም እየተሰሩ ነው። ከድሮን ጋር የተያያዙ ስራዎችም በሂደት ላይ ሲሆን በቅርቡ ይፋ እንደሚደረጉም ጠቁመዋል።

ደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ በመድፍ ፈጠራ እና በስኬታማው የሮኬት ማስወንጨፍ ሂደት ላይ ለተሳተፉ የቴክኖሎጂ ምሁራንና ተማሪዎች የእውቅና እና የምስጋና መርሀ ግብር በቅርቡ ያከናወነ ሲሆን። በመርሀ ግብሩ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ዶ/ር አነጋግረኝ ጋሻው የእውቅና መርሀ ግብሩ የተዘጋጀው በሮኬት ሳይንስ ዘርፍ ውጤታማ ስራዎች እየተከናወኑ እንደሆነ በተግባር ያሳዩትን ተመራማሪዎች፣ ምሁራን እና ተማሪዎችን በማበረታታት ለቀጣይ ስራ አቅጣጫዎችንም ማስቀመጣቸውን ዩኒቨርሲቲው በፌስቡክ ገጽ አስፍሯል።

“የቴክኖሎጂ ምሁራን እና ተማሪዎች 154ኛውን የአፄ ቴዎድሮስ ዝክረ-ሰማዕት መታሰቢያ በዓል አስመልክተው ባዘጋጁት ተጨባጭ የፈጠራ ሥራዎች ሙከራ ብዙ አካላት ተደንቀዋል” ያሉት ፕሬዚዳንቱ በተገኘው ውጤት ሳይዘናጉ የምርምር ሥራዎቻቸውን አጠናክረው እንዲቀጥሉ አሳስበዋል። አያይዘውም የሮኬት ሳይንስ ማዕከሉ ከተገኘው ውጤት በላይ በተሻለ አቅም እንዲንቀሳቀስ የዩኒቨርሲቲው ማኔጅመንት አጽንኦት ሰጥቶ እንደሚሰራ ተናግረዋል።

የዩኒቨርሲቲው ሮኬት ሳይንስ ማዕከሉ ሰብሳቢ መምህር በለጠ ጌታቸው አሁን ያደረጉት የመድፍ ፈጠራ ሥራ እና የሮኬት ማስወንጨፍ ሙከራ ጅምር መሆኑን ጠቅሰው በቅርቡ ይፋ የሚደረጉ ሌሎች የፈጠራ ስራዎች በሂደት ላይ እንደሚገኙ አመላክተዋል።

# ወቅታዊ ትንታኔ

## አገራዊ ምክክሩ እና መገናኛ ብዙሃን እንዴት ይጣመሩ?

**ታምራት ተስፋዬ**

የፖለቲካ ሳይንስ ምሁራን፤«የአስተሳሰብ ልዩነት፣ ፉክክርና የሚጋጭ ፍላጎት (Conflicting Interest) ባለባቸው አገራት ውስጥ ችግሮች በአንድ ፓርቲ፣ በአንድ ቡድን ወይንም በጥቂት ሰዎች አይፈቱም። ጥቂቶች በር ዘግተው ቢጨነቁና ቢጠበቡም መፍትሄ ሊሆኑና ሊያመጡም ፈፅሞ አይቻላቸውም። በመሆኑም ልዩነቶችን ለማጥበብም ሆነ ለማስታረቅ፣ ከተናጠል ይልቅ የጋራ ውይይት ባህልና ልምድ የግድ ነው» ይላሉ።

ኢትዮጵያ በየዘመኑ የተፈጠሩና ከዘመን ዘመን እየተሸጋገሩ የመጡ ያልተቋጩ ሃሳቦች፣ በይደር የቆዩ አለመግባባቶች እንዲሁም አገር ትቀጥል ዘንድ ቅድሚያ ተነስቷቸው የቆዩ የማያግባቡ አጀንዳዎች የተሸከመች አገር ናት። አገሪቱ ልዩነቶችን በውይይት የመፍታት የቆየ ባህል ቢኖራትም እነዚህን ባህሎች በአግባቡ የመጠቀም ልምዱ ቀስ በቀስ እየጠፋ መጥቷል። ይህ ደግሞ ችግሮች በቀላሉ ፈጣን ምላሽ እንዳያገኙ፣ ውስጥ ውስጡን እንዲብላሉና ከትላንት እስከ ዛሬ እንዲከተላት ምክንያት መሆኑ በተደጋጋሚ ሲነገር ቆይቷል። ይሑንና ከህልውና ባሻገር ስለ መፅናትና መቀጠል እንዲሁም ስለ ሁለንተናዊ እድገት ሲታሰብ እነዚህን ልዩነቶች አጀንዳዎች መፍትሄ መስጠት የግድ ያስፈልጋል።

ኢትዮጵያ ዛሬ ላይ ከትናንት ሲንከባለሉ የመጡና በአገር ግንባታ ሂደቱ ላይ የራሳቸውን እክል የሚፈጥሩ ጉዳዮችን በምክክርና ውይይት ለመፍታት ከፍ ያለ ሥራ ጀምራለች። አገራዊ የምክክር ኮሚሽን በሕግ በማቋቋምና ኮሚሽነሮችን በመሰየም ወደ ሥራ ተገብቷል። ዋናውን የምክክር ሂደት ለመጀመር የሚያስችሉ የቅድመ ዝግጅት ተግባራትም በመከናወን ላይ ናቸው።

አካታች አገራዊ ምክክሩን በተመለከተም መገናኛ ብዙኃን ነጻ፣ ገለልተኛ፣ ሚዛናዊና ወቅታዊ መረጃዎችን ተደራሽ ከማድረግ አኳያ የማይተካ ሚና አላቸው። ሁነትን ከመዘገብ የዘለለ ለውጤታማነቱ ከፍ ያለ ሚና እንዳለባቸው ይታመናል።

የኢትዮጵያ አገራዊ የምክክር ኮሚሽኝ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ የኮሚሽኑን ማቋቋሚያ አዋጅን፣ የምክክርን ጽንሰ ሀሳብና አስፈላጊነት በህትመት፣ በቴሌቪዥን፣ በራዲዮና በማህበራዊ ሚዲያ ተደራሽ እንዲሆን በማድረግ መገናኛ ብዙሃን የተለያዩ ስራዎችን ሲሰሩ ቆይተዋል። ኮሚሽኑ ከቀናት በፊትም ከመገናኛ ብዙሃን ኃላፊዎችና ተወካዮች ጋር ውይይት አካሂዷል።

በዚሁ መድረክ ላይም የኮሚሽኑ ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አርአያ፤ መገናኛ ብዙሃን ሚዲያ እውቀትን፣ እውነትን፣ ፍቅርን፣ ሠላምን፣ እድገትንና መተባበርን በቀላሉ በአፍ መፍቻ ቋንቋው በተዓማኒነት ለህዝብ የሚያደርስ መሆኑን ጠቅሰው፤ በቀጣይም ትክክለኛውን የውይይት ጽንሰ ሀሳብ፣ የአጀንዳ ቀረጻ አካሄድ፣ የውይይት ሂደትና ትግበራ፣ በየቋንቋዎቻቸው ለሕዝቡ በየወቅቱ ተደራሽ በማድረግ የኮሚሽኑ አጋር እንዲሆኑና ለምክክሩ ስኬታማነት እንዲሰሩ ጠይቀዋል።

አዲስ ዘመን መገናኛ ብዙኃን ስለ አገራዊ የምክክር መድረኩ ስኬታማነት ሚናቸው እንዴት ይቃኛል፣ ከወዲሁ ምን፣ እንዴትና በምን አግባብ መሥራትስ አለባቸው፣ የዲጂታል ሚዲው በምክክሩ ላይ የሚኖረውን ጫና ለመቋቋም ምን ሊደረግ ይገባል፣ የሚሉ ጥያቄ በማንሳት ምሁራንን አነጋግሯል።

አስተያየት ሰጪዎቹም አካታች አገራዊ ምክክር ጥያቄ ውስጥ የማይገባ አስፈላጊ ጉዳይ ስለመሆኑ ይስማሙበታል። ይሑንና ደግሞ ምክክሩ የታሰበው ውጤት እንዲገኝ በቂ ጥንቃቄና ቅድመ ዝግጅት ማድረግና ከወዲሁ መሰራት ያለባቸው የቤት ስራዎች ማከናወን እንደሚያስፈልግ ያስገነዝባሉ።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን ትምህርት ክፍል ረዳት ፕሮፌሰር ዶክተር ሳምሶን መኮንን፣ «በዓለም አቀፍ ደረጃ አገራዊ ምክክር በማድረግ የተሳካላቸው አገራት እንዳሉ ሁሉ ምክክሩ ሳይሳካላቸው የቀሩ አሉ። ለዚህ ደግሞ ሚዲያው እንደ ዋነኛ ምክንያት የሚጠቀስ ነው»ይላሉ።

«በኢትዮጵያ ሊደረግ በታሰበው አገራዊ ምክክር የሚዲያው ሚና ጉልህ ነው» የሚሉት ዶክተር ሳምሶን፣ በማህበረሰብ ደረጃ የሚደረግ ውይይት በማህበረሰባዊ ስነ-ተግባቦት የሚቃኝ ስለሆነ ሚዲያው ይህን ተግባቦት በማቀላጠፍ ረገድ የሚጫወተው አዎንታዊ ሚና ለአገራዊ ምክክሩ ስኬታማነት የበኩሉን አስተዋፅኦ ሊወጣ እንደሚችልም ይጠቁማሉ።

በሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ የጋዜጠኝነት መምህርና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሶስተኛ ዲግሪ ተማሪ የሆኑት ፍሬዘር እጅጉ፣



አቶ ፍሬዘር እጅጉ

መገናኛ ብዙሃን የተሻለ አገር እንዲፈጠር የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፣ ይሕንም በተለያየ አስተዋፅኦቻቸው ያስመለክታሉ »ይላሉ።

አካታች አገራዊ ምክክሩ አገራዊ እንደመሆኑ መጠን በተሻለና ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲከናወን ሂደቱን ከመዘገብ፣ መረጃ ከመስጠትና የተለያዩ ሃሳቦች እንዲንሸራሸሩ መደላድል መፍጠርን ጨምሮ የመሪነት ሚናን እንደሚጫወቱም ያስረዳሉ።

ምሁራኑ፣ በአገራዊ ምክክሩ የመገናኛ ብዙሃን ሚና የጎላ መሆኑን ከማስገንዘብ ባሻገር ምክክሩ የታሰበው ውጤት እንዲገኝ በቂ ጥንቃቄና ቅድመ ዝግጅት ማድረግና ከወዲሁ መሰራት ያለባቸው የቤት ስራዎች ማከናወን እንደሚያስፈልግ አፅእኖት ይሰጡታል።

ለአገራዊ ውይይቱ ሁለንተናዊ ስኬት መገናኛ ብዙሃንና ሙያተኞች ሙያዊ ስነምግባር ላይ ብቻ በማተኮር ይዘታቸውን አገራዊ ጥቅምና ሰላም ላይ ማድረግ እንዳለባቸው የሚያሳስቡት ዶክተር ሳምሶንም፣ ሚዲያው የሁሉንም ፍላጎትና ሃሳቦች ማንሸራሸር እንዳለበትም አጽእኖት ይሰጡታል።

ሚዲያውና ሙያተኛው ሙያዊ ስነ ምግባርን ማዕከል በማድረግ የአገራዊ ምክክር ሂደቶችን የሚተች፣ መንገድ የሚያሳይ፣ የታፈኑ ሃሳቦች እንዲወጡ የሚያደርግ፣ የውይይት መድረኮችን ማዘጋጀት እንዲሁም በምክክሩ ጉዳዮች ዙሪያ ሽፋኖችን በመስጠት ከአገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ጋር ተናቦ ሊሰራ እንደፈሚገባም ያስረዳሉ።

ሙያዊ ነጻነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ መገናኛ ብዙሃን የአገራዊ ምክክሩ አስፈላጊነትና ታላቅነትና ክስተትነት አምነውና ለችግሮችን መፍትሄ ይሆናል የሚለውን ሃሳብ ታሳቢ አድርገው ልዩ ትኩረት መስጠት እንደሚጠበቅባቸው የሚያስገነዝቡት አቶ ፍሬዘር በበኩላቸው፣ ሁነቱን ከመዘገብና የተለያዩ ሃሳቦችን ከማስተናገድ ባሻገርም አስፈላጊ ጉዳዮች የትኞቹ ናቸው በሚል አጀንዳ ቀርፀው ማቅረብ እንዳለባቸውም ይስማሙበታል።

ይሑንና በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ዋቢ የሚያደርጉ አስተያየት ሰጪዎች በአገራዊ ውይይቱ ላይ መገናኛ ብዙሃኑ በባለቤትነት እንደያዛቸው አካልና ሌላም ውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶች ዘርን፣ አካባቢን፣ ሃይማኖትን ወይም ሌላ ቡድናዊ እሳቤን ተከትሎ የመንጎድ አዝማሚያዎች ሊያስመለክቱ፣ ለአብነትም፣ የክልል መገናኛ ብዙኃንን፤ አጀንዳዎችን ከሚገኙበት ክልል እሳቤ ጋር ብቻ ማቆራኘት ሊታይባቸው ይችላል የሚል ስጋት ያነሳሉ።

ይሕ ስጋት የሚጋሩት ዶክተር ሳምሶንም፣ በአገሪቱ ውስጥ የሚስተዋሉ የሚዲያ ሁኔታዎች ሲቃኙ አገራዊ ፍላጎቶችን ከማንፀባረቅ ይልቅ የራሳቸውን ቡድናዊ ፍላጎቶች ማራመድ ላይ የተጠመዱ በመሆናቸው በአገራዊ ምክክሩ ችግር ሊፈጥሩ እንደሚችል ያመላክታሉ።

በመሆኑም «እንደ ኢትዮጵያ ያሉ አገራት ውስጥ የሚደረግ አገራዊ ምክክር ምን አይነት የሚዲያ ሞዴል ሊተገበር ይገባል ተብሎ ከወዲሁ ሊጤን ይገባል» የሚሉት ዶክተር ሳምሶን፣ ይህ ሲባል ግን የሚዲያ ነፃነት መጋፋት ማለት እንዳልሆነና ይልቁንም አገራዊ ጥቅሞችን ከግምት ውስጥ በማስገባት መሆኑ ሊዘነጋ እንደማይገባም ያሰምሩበታል። አገራዊ ምክክሩ ሁለንተናዊ ስኬት መገናኛ ብዙሃኑ የሚመራበት ዝርዝር መመሪያ ሰነድ ሊዘጋጅለት እንደሚገባም ይጠቁማሉ።



ዶክተር ሳምሶን መኮንን

አቶ ፍሬዘር በበኩላቸው፣ «መገናኛ ብዙሃን የየራሳቸው አላማ፣ አሰራር አቋምና እይታ ሊኖራቸው ይችላል። ይሑንና ሁሉም በአንድና በዚህ ማእቀፍ ብቻ መንቀሳቀስ አለባቸው የሚል አስገዳጅ ማእቀፍ ማስቀመጥም አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል» ይላሉ።

በአገርም ሆነ በክልል ደረጃ የሚገኙ መገናኛ ብዙሃን ከሁሉ በላይ የሙያውን መርህ እና ስነምግባርን ባከበረ መልኩ ሃላፊነታቸውን ጠብቀው መስራት እንደሚጠበቅባቸው አፅእኖት የሚሰጡት አቶ ፍሬዘር፣ ሁነቱን በመዘገብ ሂደት ከተለያየ የፖለቲካ፣ የሃይማኖትም ሆነ የብሄር ተጽእኖ ራሳቸውን ነፃ ማድረግ አለባቸውም» ይላሉ።

ምሁራኑ እንደሚገልጹት ከሆነም፣ አገራዊ ምክክሩን ውጤታማ ለማድረግ መገናኛ ብዙሃን ከቡድንና አካባቢያዊ ልሳንነት ይልቅ የሁሉም ድምጽ ሆነው፤ የጎጥ ጥቅምን ለማስጠበቅ መሣሪያ ከመሆን ወጥተው አገርን አስቀድመው ስለ አገር ክብርና ከፍታ እያሰቡ መሥራት ይጠበቅባቸዋል። ለዚህ ሥራቸው ደግሞ ራሳቸውን ገለልተኛ ማድረግና ለየትኛውም ቡድን ፍላጎት መሳካት ከሚደረግ ጥረት ነጻ ማውጣት ይኖርባቸዋል።

ይሑንና አሁን ባለው ሁኔታ ይሕን በቀላሉ ማድረግ ይቻላል ወይ ተብሎ መጠየቁ አይቀሬ ነው። ለዚህ ምላሽ የሚሠጡት አቶ ፍሬዘር፣ በመገናኛ ብዙሃንና በጋዜጠኝነት ሙያ አንዱ መሰረታዊ ጉዳይ የህግ ማእቀፍ ስለመሆኑ ይጠቁማሉ።

በዚህ ሂደት አሁን ያለው የህግ ማእቀፍ ክልል መገናኛ ብዙሃን በነጻነት ከፖለቲካ ፓርቲ ከልሎች ጣልቃ ገብ አካላት ገለልተኛ ሆነው መስራት የሚችሉበትን አግባብ ለመፍጠርም አዋጆች፣ ህጎችና አደረጃጀታቸው መፈተሽ በተለይም ከፖለቲካም ሆነ በኢኮኖሚ ተፅእኖ ነጻ የሆነ አደረጃጀት እንዲይዙ ማድረግ ያስፈልጋል» ይላሉ።

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ መሐመድ ኢድሪስ፤ መገናኛ ብዙሃን የምክክር መድረኩ ውጤታማ እንዲሆን በባለቤትነት መንፈስ ሊሰሩ እንደሚገባ አጽኖት ይሰጡታል። መገናኛ ብዙሃን በሌሎች አገራዊ ጉዳይ ላይ ያሳዩትን ወገንተኝነት በአገራዊ ምክክሩ ላይም መድገም በተለይም ለጉዳዩ ሰፊ ሽፋንና ከመስጠት ጀምሮ ተግባቦት ላይ ጠንካራ ሥራ መሥራት እንዳለባቸውም ያስገነዝባሉ።

«አገራዊ ምክክሩን ውጤታማ ለማድረግ በዕውቀት ላይ የተመሰረተ መረጃ አሰጣጥ የግድ ነው»የሚሉት ዳይሬክተሩ፣ መገናኛ ብዙኃን የሂደቱን ከሚያደናቅፍ መንገድ ተቆጥበው መሥራት እንዳለባቸው አፅእኖት ይሰጡታል።

«በምክክር ሂደቱ ወቅት በሚካሄዱ ውይይቶች ላይ የሚነሱ ሃሳቦችን ለማንቋሸሽና ለመግፋት ከሚደረጉ ጥረቶች፤ በጽንፈኝነት የሚወጡ ሃሳቦችን ሌሎች ላይ ከማራገፍ እንዲሁም የአንድን አካል ሃሳብ ባልተገባ መንገድ ከመጠቀም የመቆጠብ ግዴታ አለባቸውም» ይላሉ።

የምክክር ኮሚሽኑም ለመገናኛ ብዙኃን ወቅቱን የጠበቀ መረጃ በአስፈላጊው ሰዓት በማቅረብ ተደራሽ የመሆን ግዴታ እንዳለበት ጠቁመው፣ መገናኛ ብዙኃኑ ህብረተሰቡን በውስጥ ሃሳብ ከማጠርና አስተሳሰቡን ከመገደብ መቆጠብ፣ ብዝሃነትን የሚቀበሉና ጽንፈኝነትን የማያራግቡ ሆነው ምክክሩን በአግባቡ ማስተላለፍ ይኖርባቸዋል» ነው ያሉት።

በአገራዊ ምክክር ሂደቱ መገናኛ ብዙሃኑም በጽኑ ዲሲፕሊን የራሳቸው አጀንዳ ከመስጠትና አላስፈላጊ ጥብቅ መቆጠብ እንዳለባቸው ያስገነዘቡት ዋና ዳይሬክተሩ፣ ተቋማቸውም በአገራዊ ምክክሩ ላይ የሚተላለፉ ዘገባዎችን መሰረት በማድረግ በመገናኛ ብዙኃኑ አሰራር ላይ ቁጥጥር እንደሚያደርግ በየጊዜው ግብረ መልስ እንደሚሰጥ ነው ያስታወቁት።

ከመደበኛ የመገናኛ ብዙሃን አውታሮች ባሻገር በተለይ የዲጂታል ሚዲያው ለአገራዊ ውይይቱ ከባድ ራስ ምታት እንደሚሆን የሚጠቁሙና ከወዲሁም መፍትሄ ሊፈለግለት ይገባል የሚል አቋም ያላቸውም በርካቶች ናቸው።

አቶ ፍሬዘር እጅጉም፣«በመደበኛው መገናኛ ብዙሃን መፈፀም የማይቻሉ ተግባራት በዲጂታል ሚዲያ ሊፈፀሙ ይችላሉ። ሀሰተኛ እንዲሁም ፀብ ቀስቃሽ የሆኑና በጥላቻ የተሞሉ መረጃዎችን በስፋት የሚሰራጭባቸው መድረኮችም ሲሆኑ ይስተዋላል» ይላሉ።

ይሕ ደግሞ ለአገራዊ ውይይቱ ፈተና እንደሚሆን ይስማሙበታል። እንደ መደበኛው ሚዲያ እነዚህን በቀላሉ መቆጣጠር እንደማይቻል የሚጠቁሙት አቶ ፍሬዘር፣ ሁነኛ መፍትሄውም መደበኛውን መገናኛ ብዙሃን ማጠናከር መሆኑን ያስገነዝባሉ።

እንደ አቶ ፍሬዘር ገለጻ፣ መደበኛው መገናኛ ብዙሃን ጠንካራ ሆነው መውጣትና እውነተኛ መረጃ ለህዝብ ተደራሽ ማድረግ በቻሉ ቁጥር በዲጂታል ሚዲያው የሚሠራጨው ሃሰተኛ መረጃ ይዳከማል። መደበኛ መገናኛ ብዙሃን እንዲጠናከሩና እንዲስፋፉ ለማድረግ ደግሞ የማትጊያ ስልቶችን ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል።

ከሁሉ በላይ መደበኛ መገናኛ ብዙሃን መረጃ የማግኘት መብትን በእጅጉ ቀላልና ቀልጣፍ ማድረግ የግድ እንደሚል የሚያስገነዝቡት አቶ ፍሬዘር፣ ማህበራዊ ሚዲያውን ከመቆጣጠር ባሻገር ዜጎች መረጃ በሚመለከት አስተዋይ፣ ጠንቃቃና ፈታሽ እንዲሆኑና በተሳሳተ አረዳድ፤ ያልተፈለገ ተግባር እንዳይፈፅሙ በተለይም የመገናኛ ብዙሃን መሰረታዊ እውቀት ወይንም ሚዲያ ሊትሬሲን ማጎልበት ናስልጠና መስጠት እንደሚያስፈልግም ሳያስገነዝቡ አላለፉም።

ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ሹመቴ ይግዛውም ዲጂታል ሚዲያው ወቅታዊ የአገር ፈተና መሆኑን ይስማሙበታል። «ባለፉት 30 ዓመታት የተሠሩ የፖለቲካ ትርክቶችና የተሠሩ ሥራዎች ለማኅበራዊ ትሥሥር ገፆች ትልቅ ግብዓት ወደ መሆን አዝማሚያ ሄደዋል። ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም አሸባሪው ሕወሓትን ጨምሮ በአገር ውስጥና ከአገር ወጪ ያሉ የኢትዮጵያን መልካም ነገር የማይፈልጉ አካላት በዲጂታል መንገድም ሆነ በአካላዊ ጦርነት ኢትዮጵያን ለማጥቃት ያላሰለሰ ጥረት እያደረጉ ይገኛሉም» ይላሉ።

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለጻም፣ ዲጂታል ሕወሓት የዲጂታል ጦርነቱን በተለያየ መንገድ እየተገበረ ነው። ለአብነትም ኦሮሞ ሳይሆኑ የኦሮሞ ሥም ገፆችን በመክፈት፤ አማራ ሳይሆኑ የአማራ ሥም የያዘ ገፅ በመክፈት የብሔር ጉዳዮችን አንስቶ በመሳደብና ተቆርቋሪ በመምሰል በሐሰተኛ ገፅ ተጠቅመው ከፍተኛ የሆነ የመረጃ ማዛባት ጦርነት እያካሄዱ ነው።

በተጨማሪም በአርቲስቶች፣ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችና በሌሎች ታዋቂ ሰዎች ሥም በርካታ ሐሰተኛ የትሥሥር ገፆች ተከፍተው ሲሠሩ በክትትል ተደርሶባቸው በሕግ የተጠየቁና ውሳኔ የተላለፈባቸው አሉ። ቁጥራቸው በርከት ያለ የሐሰተኛ መረጃ አሰራጮችና የሐሰተኛ ገፅ ተጠቃሚዎች በክስ ሂደት ላይ ይገኛሉ።

ሐሰተኛ የትሥሥር ገፆች ብቻ ሳይሆኑ ትክክለኛ አካውንቶች ሆነው ጭምር ትክክለኛ ያልሆኑ መረጃዎችን የሚያሠራጩ እንዳሉ የሚገለጹት ዶክተር ሹመቴ፤ ዲጂታል ሚዲያዎችን በአግባቡ የመጠቀም ግንዛቤ በማኅበረሰቡ ዘንድ እምብዛም መሆኑ ለሚነሳው ሐሰተኛ መረጃ ጥሩ አጋጣሚ እንደፈጠረለት ይጠቁማሉ።

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የራሱ የሆነ መሥፈርት አውጥቶ ሰፊ ክትትል እያደረገ እንደሆነና በሕግ የማስጠየቅ አጠናክሮ እንደሚቀጥል ጠቅሰው፣ ዋናው ነገር ግን ከገበያ የተገኘ ሁሉ እንደማይገዛ እንዲሁ መረጃዎች ሁሉ አይገበዩም፤ ህብረተሰቡ ምንጫቸው መጣራት ይኖርበታል። ይህ ሲደረግ የሐሰተኛ መረጃዎች ሥርጭት እና የሚያደርሱት ጉዳት እንዲቀንስ ይሆናል ነው»ያሉት። ፡

«ከማህበራዊ ሚዲያ ጋር ተያይዞ ያለውን ችግር ለመቅረፍ ጠንካራ ቁጥጥር ለማድረግ ዝግጅት እየተደረገ ነው » የሚሉት የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ መሐመድ ኢድሪስ በበኩላቸው። እንደ ተቋም እነዚህን የመገናኛ ብዙኃንና የማህበራዊ ሚዲያዎችን መቆጣጠር የሚያስችል ረቂቅ ሕግ ተዘጋጅቶ ጉዳዩ ለሚመለከተው የፍትህ ሚኒስቴር መቅረቡንና ሲፀድቅም ተግባራዊ እንደሚደረግ አመላክተዋል።

ማህበራዊ
# ሴቶች

# የስኬታማ ሴቶች የሥኬት ምስጢሮች

**ሰላማዊት ውቤ**

ባለፉት አራት የለውጥ ዓመታት ሴቶች ከቀደሙት ስርዓቶች ጋር ሲነፃፀር የተሻለ ቦታ ላይ መቀመጥ ችለዋል። በ2011 ዓ.ም 20 አባላት ባሉት የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ የሚኒስትሮች ካቢኔ 10ሩን ሴት ሚኒስትሮች በማድረግ የጾታ ስብጥሩን በአጭር ጊዜ ውስጥ ማመጣጠን ተችሎ የነበረ መሆኑ ሴቶች አሁን የደረሱበትን ደረጃ ያመለክታል። ቀስ በቀስ ፖለቲካዊ ተሳትፏቸው እየጨመረ፤ አቅማቸውም እየጎለበተ መምጣት ችሏል። በየተሰማሩበትም መስክ አያሌ ስኬቶችን ለማስመዝገብ በቅተዋል።

የስነ ልቦና ባለሙያዎች እንደሚናገሩት ሴቶችን ለስኬት ከሚያበቁት ዋንኛው በራሱ ለስኬት ሊበቁ የሚችሉበትን መስክ ማግኘት መቻላቸው ነው። ሌላው ሴቶች ከወንዶች ጋር ሲነፃፀሩ ከወንዶች ይልቅ ጠንቃቃ መሆናቸው ነው። እንደ ስነ ልቦና ባለሙያዎቹ ምክረ-ሀሳብ በርግጥ ሴቶች በባህርያቸው ከወንዶች በተሻለ ጠንቃቃ ናቸው። ከነገሮች ጋርም ቢሆን ቶሎ የመላመድ ችሎታ አላቸው። አዳዲስ ነገሮችን ለማወቅና ለማግኘት ጉጉና ራሳቸውን በፍጥነት የሚያዘጋጁም መሆናቸውን የስነ ልቦና ባለሙያዎቹ ይናገሩላቸዋል። አስቸጋሪ ሁኔታዎችን በመቋቋም ተፎካካሪ መሆንን ይችሉበታልም ይሏቸዋል።

በአብዛኛው ሴቶች ከወንዶች ይልቅ በተሰማሩበት የሥራ መስክ ፈጥነው ስኬት መጨበጥ የሚችሉት በነዚህ ዓይነቶቹ ወሳኝ ነጥቦች መሆኑንም የስነ ልቦና ባለሙያዎቹ ይመሰክሩላቸዋል። ዘመናዊና በቂ ዕውቀት ከተካበተ ልምድ ጋር መቅሰም ሴቶችን ፈጥኖ ለስኬት የሚያበቃ ተደማሪ ምስጢር መሆኑንም ባለሙያዎቹ ይጠቁማሉ። በዘንድሮ ዓመት መጀመርያዎቹ ወራቶች አካባቢ 100 የአፍሪካ ተጽዕኖ ፈጣሪ ሴቶችን ለስኬት ያበቁት እነዚሁ ምስጢሮች አይደሉም ማለት አይቻልም።

መቀመጫውን በአህጉራችን አፍሪካ ያደረገውና አቫንሴ ሚዲያ የተሰኘው ድርጅት በዚሁ በዘንድሮ ዓመት ለእነኚህ ድንቅ ሴቶች ዕውቅና ሊሰጥባቸው ያስቻሉትም በተሰማሩበት ልዩ ልዩ የሥራ መስኮች ስኬትን ማጎናፀፍ ያስቻሉ የስኬት ምስጢሮች ናቸው። አቫንሴ ሚዲያ በተሰማሩበት ልዩ ልዩ የሥራ መስኮች ስኬትን መጎናጸፍ ለቻሉ አፍሪካዊያን ሴቶች በየዓመቱ ዕውቅና ይሰጣል፡ ፡ የሚሰጠውም በእነዚህ መስፈርቶች በማወዳደርም ነው። ሚዲያው ላለፉት ሶስት ተከታታይ ዓመታትም ዕውቅና የመስጠት ተግባሩን ሲያከናውን የቆየው በዚህ መልኩ ነው። አቫንሴ ሚዲያ እንደ አውሮውያኑ ዘመን አቆጣጠር በ2021 በተመሳሳይ በተለይ የአመራርና አፈጻጸም ክህሎትን፣ በግል ያስመዘገቡት ስኬትና ዕውቀትን የማጋራት ቁርጠኝነት የተላበሱ፤ እንዲሁም የተለመደና ምቹ ያልሆነ አሰራር ስርዓት በመቀየር ረገድ ተቋማዊ ለውጥ ያመጡ በሚል ያስቀመጣቸውን እነዚህን ስድስት ብቃት አጎናፂፊ ምስጢሮች የተላበሱ ዝርዝር መስፈርቶች አሟልተው የተገኙበትና ከመላው አፍሪካ አገራት በእጩነት የቀረቡበት ምርጫ አካሂዶ ነበር።

ድርጅቱ በዚህም መሰረት ስኬታማና ውጤታማ የሆኑ 100 ተጽዕኖ ፈጣሪ አፍሪካዊ እንስቶችን በመለየት ስም ዝርዝራቸውን 100women.avancemedia.org በተሰኘ ይፋዊ ድረ-ገጹ አስታውቋል፡፡ አቫንሴ ሚዲያ ዘንድሮ ባካሄደው የምርጫ ሂደት አገራችንን ወክለው በእጩነት ከቀረቡት እንስት ኢትዮጵያውያን መካከል የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ርዕሰ-ብሔር ሳህለወቅር ዘውዴ፣ የኢትዮ ቴሌኮም ዋና ስራ አስፈጻሚ ፍሬህይወት ታምሩ፤ እንዲሁም የሶልሪቤል ጫማ ፋብሪካ መስራችና ስራ አስስኪያጅ ወይዘሮ ቤተልሔም ጥላሁን በዝርዝሩ ውስጥ ስማቸው መካተቱን ይፋ ያደረገበት ሁኔታ እንደነበር ይታወሳል፡፡ ይህም አገራችንን በጎ ገጽታ እንድትላበስ የበኩሉን እገዛ አድርጓል፡፡ ከበጎ ገጽታው ባሻገርም ሌሎች የአገራችን ሴቶችን ለስኬት በማነሳሳትና በማብቃት አርአያ እንደሚሆንም አያጠያይቅም፡፡



**የመጀመሪያዋ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሴት ፕሬዚዳንት አምባሳደር ሳህለወርቅ ዘውዴ**

ይኼን ካልን ዘንዳ በአቫንሴ ሚዲያ ተጽዕኖ ፈጣሪነታቸው ተረጋግጦ ዕውቅናን ማግኘት ከቻሉት ሴቶች መካከል የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሆነው አገርና ሕዝባቸውን እያገለገሉ ሥላሉት ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ የተወሰነ ልንነግራችሁ ወደድን፡፡ አምባሳደር ሳህለወርቅ ዘውዴ በወርሃ የካቲት 1942 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ነው የተወለዱት። የመጀመርያ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምርታቸውን ያጠናቀቁት በሊሴ ገብረማርያም ትምርት ቤት ሲሆን፤ የፈረንሳዩ ሞንተፔለ ዩኒቨርሲቲ የተፈጥሮ ሳይንስ ምሩቅ ናቸው። አማርኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ እና እንግሊዘኛ አቀላጥፈው ይናገራሉ። ቁጥር በሌላቸው ዓለም አቀፍ መድረኮች በእነዚህ ቋንቋዎች ንግግር አድርገዋል፡፡ አምባሳደሯ ንግግር አዋቂና ብልህ ሴት በመሆናቸው ንግግር ባደረጉበት መድረክ ሁሉ ረጋ ብሎ አረፍተ ነገሮችን እያስረገጡ ጥዑመ ዜማ በመላበስ ጥርት ብሎ የሚንቆረቆረው ድምፃቸው ሳይሰለቹ እንዲደመጡና ንግግር ባደረጉ ተብለው እንዲናፈቁ ሲያደርጋቸው ቆይቷል፡፡ አሁንም እንደዛው።

አምባሳደር ሳህለወርቅ ዘውዴ ለኢትዮጵያ እንደ ውጪ አገር አገልግሎት ሰራተኛ እ.ኤ.አ ከ1989 እስከ 1993 ተቀማጭነታቸውን ሴኔጋል በማድረግ የማሊ፣ የኬፕ ቨርድ፣ የጊኒ ቢሳዎ፣ የጋምቢያና የጊኒ አምባሳደር በመሆን አገልግለዋል። እኤአ ከ1993 እስከ 2002 ደግሞ በጅቡቲ አምባሳደር ሆነው የሰሩ ሲሆን በወቅቱ የምሥራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግሥታት ድርጅት (ኢጋድ) ቋሚ ተወካይም ነበሩ። እኤአ ከ2002 እስከ 2006 በፈረንሳይ አምባሳደር በመሆን አገልግለዋል፡፡ እንዲሁም የተባበሩት መንግሥታት የትምህርት የሳይንስና የባህል ተቋም ተወካይ ሆነው ሰርተዋል። በተባበሩት መንግሥታት ልዩ መልዕክተኛ ውስጥ የተቀናጀው የሰላም አስከባሪ ኃይል ተወካይ በመሆን በሴንትራል አፍሪካ (BINUCA) ኃላፊ በመሆንም ያገለገሉበት ዳጎስ ያለ ታሪክ አላቸው።

በአፍሪካ ሕብረት ውስጥና በተባበሩት መንግሥታት የኢኮኖሚ ኮሚሽን ውስጥም የኢትዮጵያ ቋሚ ተወካይ ሆነው ማገልገላቸው ይነገራል፡፡ አምባሳደር ሳህለወርቅ በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ውስጥም የአፍሪካ ጉዳዮች ዳይሬክተር ጄነራል ሆነው ሰርተዋል። እ.ኤ.አ በ2011 የተባበሩት መንግሥታት ዋና ፀኃፊ የነበሩት ባን ኪሙንም በኬኒያ የተባበሩት መንግሥታት ዳይሬክተር ጄነራል አድርገው ሾመዋቸው ያገለገሉበት ሁኔታ መኖሩን ሰነዶች ያወሳሉ። በተባበሩት መንግሥታት ዋና ፀኃፊ አንቶኒዮ ጉቴሬስ በአፍሪካ ሕብረት ልዩ ተወካይ እንዲሁም በአፍሪካ ሕብረት የተባበሩት መንግሥታት ቢሮ ኃላፊ ሆነው ተሾመዋል። አምባሳደር ሳህለወርቅ ጥቅምት ፲፰ ቀን ፳፻፲፩ ዓ.ም የኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት ሆነው ተመርጠዋል። በፕሬዚዳንትነት ሚና ለማገልገል የመጀመርያዋ ሴት መሆናቸውንም ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡

አምባሳደር ሳህለወርቅ ሁለት የስድስት ዓመት ውል እንደሚያገለግሉ የሚጠበቅ ሲሆን፤ በአሁኑ ጊዜ በአፍሪካ ውስጥ አምባሳደር ሳህለወርቅ ብቻ ናቸው ሴት የአገር መሪ። ከሳቸው በፊት ኢትዮጵያ የነበራት አንድ ሌላ ሴት የአገር መሪ ቢኖሩ የዳግማዊ አፄ ምኒልክ ልጅ ንግሥት ዘውዲቱ እንደነበሩ ሰነዶች ይጠቅሳሉ፡፡ ሳህለወርቅ በአቫንሴ ሚዲያ ዕውቅናውን ማግኘት የቻሉት በእነዚሁ አስተዋጾአቸው መሆኑን ከሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሕዝብ ግንኙነት ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

በተመሳሳይ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት “አምባሳደር ሳህለወርቅ ዘውዴ ማን ናቸው?” ሲል በሰራው ዘገባ እንዳመለከተው፤ ፈረንሳይ በሚገኘው ሞንፔሌር ዩኒቨርሲቲ የተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርታቸውን የተከታተሉ ሲሆን፤ አማርኛ፣ ፈረንሳይኛና እንግሊዝኛ ቋንቋን አቀላጥፈው መናገር ይችላሉ፡፡ የበዛውን የሕይወት ጉዞና የሥራና የትምህርት እርምጃዎቻቸውን አጠቃልሎ ሲያቀርብም፤ አምባሳደር ሳህለወርቅ በአምባሳደርነትና በተለያዩ ኃላፊነቶች በታላላቅ አለማቀፋዊ ተቋማት አገልግለዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ የኢፌዴሬ ፕሬዚዳንት ሆነው ከመሰየማቸው አስቀድሞ፤ በአፍሪካ ህብረት የተመድ ዋና ፀሀፊ አንቶኒዮ ጉተሬዝ ልዩ ረዳት እና በአፍሪካ ህብረት የተባበሩት መንግስታት ኃላፊ ሆነው እያገለገሉ ነበር፡፡ ከዛም ቀደም ብለው ከ 1989 እስከ 1993 በሴኔጋል፣ ኬፕቨርዲ፣ ጊኒቢሳው፣ ጋምቢያና ጊኒ የኢትዮጵያ አምባሳደር ሆነው አገራቸውንና ሕዝባቸውን አገልግለዋል፡፡

በተመሳሳይ፣ ከ 1993 እስከ 2002 በጅቡቲ የኢትዮጵያ አምባሳደርና የኢጋድ ቋሚ መልዕክተኛ፣ ከ 2002 እስከ 2006 በፈረንሳይ የኢትዮጵያ አምባሳደር፣ በዩኔስኮ የኢትዮጵያ ቋሚ መልዕክተኛ እና የቱኒዝያና ሞሮኮ ተጠሪ ሆነው ያገለገሉ ሲሆን፤ በመካከለኛው አፍሪካ ሪፐብሊክ የተባበሩት መንግስታት የተቀናጀ ሰላም ግንባታ ቢሮ ልዩ ተወካይና ኃላፊ ሆነውም ሰርተዋል፡፡

ፕሬዚዳንት፣ ሳህለወርቅ በአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን እና በአፍሪካ ህብረት የኢትዮጵያ ቋሚ መልዕክተኛ እንዲሁም በኢፌዲሪ ውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር የአፍሪካ ጉዳዮች ጀነራል ዳይሬክተር በመሆን በከፍተኛ ኃላፊነት ሰርተዋል፡፡ በ2011 በናይሮቢ የተባበሩት መንግስታት ቢሮ ዳይሬክተር ጄኔራል በመሆን በወቅቱ የተመድ ዋና ፀሀፊ ባን ኪ ሙን ተሹመው ያገለገሉት ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ፤ በተመድ ከዋናና ምክትል ዋና ፀሀፊነት ቀጥሎ ያለውን ከፍተኛ የአመራር እርከን ያገኙ የመጀመሪያዋ ሰውም ናቸው፡፡

ይህ ከፍ ያለ የትምህርት ዝግጅታቸው እና የሥራ ልምድና ክህሎታቸው ታዲያ የኢትዮጵያ ርዕሰ ብሔር ሆነው እስከመሰየም አድርሷቸዋል፡፡ በዚህም ዘርፈ ብዙ ተግባራትን በመፈጸም ለአገራቸው ሁለንተናው ከፍታና ብልጽግና እርሳቸው የሚጠበቀውን ሁሉ እያበረከቱ ያሉ ሲሆን፤ በተለይ ለሴት ልጆች ከፍታ በልዩ ትኩረት እየሰሩ ይገኛል፡፡ ለዚህ ደግሞ ፕሬዚዳንቷ ፕሬዚዳንት ከሆኑ በኋላ ለአገሪቱ የሕዝብ ተወካዮችና የፌዴሬሽን ምክር ቤቶች ባደረጉት የመጀመሪያ ንግግር ለሴቶች ድምጽ ለመሆን ቃል ገብተው ሥራ የመጀመራቸው ምስጢር ስለመሆኑ ይነገራል፡፡

የፕሬዝዳንቷ መመረጥ ተከትሎም በኢትዮጵያ ውስጥ የሴቶች ውክልና እየጨመረ መምጣቱን የሚናገሩም ጥቂት አይደሉም፡፡ ለታዳጊና ወጣት ሴቶች በስኬታማ ለሴቶች እንዲሰጥ አቅጣጫ ያስቀመጡበትና ሲተገበር የቆየውም ፕሬዚዳንታዊ ሜንተርሺፕም የዚሁ ሥራቸውና ለሴቶች ከፍ ያለ ቦታ መስጠታቸው ማሳያ ተደርጎም ይነገራል፡፡ ፎርብስ ባወጣው 100 የዓመቱ (2020) ተጽዕኖ ፈጣሪ ሴቶች ዝርዝር ውስጥ ሲያካትታቸውም እነዚህንና ሌሎች በርካታ የስኬት ጉዟቸው፤ የውጤት መንገዳቸውን ከግምት በማስገባት ነው፡፡

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

ኃይለማርያም ወንድሙ

**በዛሬው የአዲስ ዘመን ድሮ ዓምዳችን ጋዜጣው በ1963 ዓ.ም ይዟቸው ከወጣ ወንጀልና ፍትህ ነክ ዘገባዎች መካከል ብታነቧቸው ብለን የተወሰኑትን ዘገባዎች መርጠን ይዘን ቀርበናል። መልካም ንባብ።**

### በጆንያ ታፍና የተወሰደችው ልጅ አሰላ ትገኛለች

አሰላ (ኢ-ዜ-አ-) በጆንያ ውስጥ ታፍና ከቤቷ የተወሰደችው ፋጡማ መሐመድ ለሁለት ወር ያህል በማታውቀው ቀበሌ ስትንከራተት ከሰነበተች በኋላ ትናንት አሰላ ከተማ ደርሳ በጠ/ግዛቱ ፖሊስ መምሪያ ተገኘች።

፲፯ ዓመት ዕድሜ ያላት ፋጡማ መሐመድ አዲስ አበባ ካሳ ገብሬ ሠፈር የምትኖር መሆኗን ለፖሊስ መምሪያ በሰጠችው ቃል ማረጋገጧን ረዳት ዋናው አዛዥ ገልጠዋል።

መልኳ ጠይም፤ ዐይነ ትንንሽና ጥርሰ ፍንጭት የሆነችው ፋጡማ መሐመድን አንድ የማታውቀው ሰው ከመኖሪያ ቤቷ ውስጥ በከረሜላ አባብሎ እንድትወጣ ካደረገ በኋላ አፏን በጨርቅ አፍኖና በጆንያ ከትቶ በጭነት መኪና የወሰዳት መሆኑን የጠ/ግዛቱ ፖሊስ ረዳት አዛዥ ኮሎኔል ኃይሌ ጫኔ ገልጠዋል።

ፋጡማ በዚሁ ሁኔታ ከአንዱ ቀበሌ ወደ ሌላው ቀበሌ ከመንገደኞች ጋር ስትዘዋወር አሩሲ ጠ/ግዛት ጭላሉ አውራጃ ዟይ ዱግዳ ከተባለው ከተማ ደረሰች። እዚያም በመንገላታት ላይ እንዳለች አንድ ሰው ይህን መንገድ ይዘሽ ወደ አሰላ ሒጂ ብለው ስለመከሩኝ ወደዚህ መጣሁ ብላ ለፖሊስ ጣቢያ በሰጠችው ቃል ገልጣለች።

የፋጡማ ወላጆች ፋጡማን አሩሲ ጠ/ግዛት ፖሊስ መምሪያ ድረስ መጥተው ሊያገኟት መቻላቸውን ረዳት አዛዡ በተጨማሪ ገልጠዋል።

ይሁንና ፋጡማ በማታውቀው ሰው በመኪና ታፍና ከተወሰደች በኋላ የት ቦታ እንደወረደች ወይም እንደተጣለች አዛዡ አላብራሩም።

**( ሚያዝያ 22 ቀን 1963 ዓ.ም)**

### የ10 እና የ25 ሳ.ባስ አልቤርጎች ተከሰሱ

የባህር ዛፍ አጣና እንደቆጥ እየረበረቡ ፤በላዩ ላይ ጆንያ ደልድለው አሮጌ ባና እየደረቡ በአንድ ክፍል ቤት እስከ ፴፪ ሰዎች እያስተኙ ፤በአንድ ሌሊት ከ፲ እስከ ፳፭ ሳንቲም ለአንድ ሰው የሚያከራዩ ፲፬ ሰዎች ተከሰሱ።

ተከሳሾቹ አልቤርጎዎቹን አዲስ አበባ በአሜሪካ ግቢ ፤በጌሾ ሠፈር፤በራጉኤል ቤተክርስቲያን አካባቢ ያለፈቃድ ለብዙ ዓመቶች ሲያከራዩ ቆይተው ሰሞኑን በምዕራብ ጤና ጥበቃ መሥሪያ ቤት ተከታታይነት ተይዘው መጋቢት ፳፫ ቀን ፯ ወረዳ ፍርድ ቤት ቀርበዋል።

በሦስቱ ቀበሌዎች እስከ ብዙ የአጠና ርብራብ ቆጦች የሚገኙ መሆናቸው ሲገመት በአንድ ሌሊት ቁጥራቸው የበረከተ ሰዎች ለማስተናገድ የሚችሉ መሆናቸውን የምዕራብ ጤና ጥበቃ ሹም አቶ ተረፈ ኃይሉ ባደረጉት መከታተል የደረሱበት መሆናቸውን ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ በሰጡት ዜና ገልጠዋል።

አሥራ አራቱ አልቤርጎዎች ውስጥ የሚተኙት ሰዎች መግባት የሚጀምሩት ከሌሊቱ ፬ ሰዓት ሲሆን ፤ወድቅቱን በሙሉ ሲወጡና ሲገቡ ቢያድሩም ቀኑን ተኝተው ቢውሉ ሁሉም ነገር ነፃ ነው። ዜና አቅራቢው ለመጎብኘት በሔደበት ጊዜ አንዳንዶቹ ቤቶች ተዘግተው የተኙትን ሰዎች በጭላንጭል ተመልክቷል።

ለማነጋገር ፈልጎ መልስ የሚሰጥ አልተገኘም። ወዲያው ኩሼ ሆነ። በአቅራቢያው የሚገኙ አንዳንድ ኗሪዎች እንዳመለከቱት፤ በነዚህ አልቤርጎዎች ውስጥ ዘወትር ሌሊቱን ጭፈራና ዘፈን ይሰማል። ሁልጊዜ ደስታ ነው። ጥቂትም ቆይቶ ድብድብና ሁካታ ይስተጋባል። ከሌሊቱ ፲ ሰዓት ሲሆን ፍጹም ጸጥታ ይሆናል። አብዛኛው ጊዜ በቀን ሲወጣና ሲገባ የሚታይ ሰው የለም በማለት አስረድተዋል።

አቶ ተረፈ እንደገለጡት አልቤርጎዎቹ ከተቋቋሙ አያሌ ዓመታት ሆኖዋቸዋል። በሰው ሕይወት ላይ ጠንቅ የሚያስከትሉና ለሠፈር ጸጥታ የሚያውኩ መሆናቸው የተደረሰባቸው በአሁኑ ዓመት በተደረገው የጽዳት ዘመቻ መንገዶች ስለተከፈቱ አካባቢውን ለመቆጣጠር በምንዘዋወርበት ጊዜ ደርሰንበት ባለ አልቤርጎዎቹን ከሰናቸው ፍርድ ቤት ቀረቡ። ባለ አልቤርጎዎቹ ፈቃድ አውጥተው ቤታቸውን አጽድተው በደንበኛ አልጋዎች ካልሠሩ በአሁኑ ይዞታ እንዲቀጥሉ የማይፈቀድ መሆኑን አስረድተዋል።

**( መጋቢት 29 ቀን 1963 ዓ.ም)**

### ቆማ የተገኘችው መኪና አሁንም ባለቤት አላገኘችም

አንዲት ባለቤቷ ያልታወቀ ቁጥሯ 2684 አዲስ አበባ የሆነ ቮልክስዋገን መኪና በናዝሬት ከተማ አቅራቢያ ወደ ወንጂ በሚወስደው መንገድ ላይ ቆማ መገኘቷንና የኔናት ባይ ጠፍቶ አሁንም በናዝሬት ፖሊስ ጣቢያ የምትገኝ መሆኗን የሸዋ ፖሊስ የማስታወቂያ ክፍል ገለጠ።

መኪናዋ በዚሁ ሥፍራ ቆማ የተገኘችው በ20 /7/63 ዓ/ም ነው። እስካሁንም ድረስ ወሳጅ ባለቤት አለመገኘቱ ታውቋል። በዚህም ምክንያት በክፍሉ ፖሊስ አማካይነት ከቆመችበት ቦታ ተነስታ ወደ ናዝሬት ፖሊስ ጣቢያ ተወስዳ በዚያ ትገኛለች። ሁኔታውንም በይበልጥ ለማረጋገጥ እንዲቻል ፖሊስ ጉዳዩን በመከታተል ላይ ይገኛል።

ነገር ግን የመኪናዋ ባለቤት ከተገኘ ከተጠቀሰው ፖሊስ ጣቢያ ድረስ ሔዶ ለመውሰድ መቻሉ ተገልጧል። አንዳንድ ጊዜ በአቃቂም ሆነ በደብረ ዘይት መንገድ ባለቤታቸው ያልታወቀ መኪናዎች እየቆሙ እንደሚገኙ ታውቋል። ይህችም መኪና እስካሁን ድረስ ወሳጅ ባለቤት ያጣቸው ምናልባት በስርቆት ተወስዳ ይሆናል ሲል አንድ የማስታወቂያ ክፍል ቃል አቀባይ አስረድቷል።

**(ሚያዝያ 1 ቀን 1963 ዓ.ም )**

# ዓለም አቀፍ

## የአሜሪካ ፖሊስ ተያይዘው የጠፋትን እስረኛ እና የማረሚያ ቤት ፖሊስ እያፈላለገ ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር

የአላባማ ግዛት ፖሊስ በግድያ ወንጀል የተከሰሰ እስረኛ እና ከእርሱ ጋር አብራው የጠፋች የማረሚያ ቤት መኮንንን እያሰሰ ነው።

እስረኛ ኬሲ ዋይት የማረሚያ ቤቱ መኮንን ከሆነችው ቪኪ ዋይት ጋር ለመጨረሻ ጊዜ አብረው ቢታዩም በኋላ ግን ሁለቱ ግለሰቦች የት እንደገቡ አልታወቀም።

የማረሚያ ቤቱ መኮንን ቪኪ ዋይት እስረኛውን ኬሲ ዋይትን ለአዕምሮ ጤና ግምገማ እየወሰደችው እንደነበር ተናግራ የነበረ ሲሆን፣ በኋላ ላይ ግን ባለሥልጣናት የአዕምሮ ጤና ግምገማው ቀድሞ ፕሮግራም የተያዘለት እንዳልነበር ደርሰውበታል።

ባለሥልጣናት መኮንኗ፣ እስረኛው እንዲያመልጥ ረድታው አልያም ደግሞ በግለሰቡ ታግታ እንደሆነ ለማጣራት ምርመራ እያካሄዱ ነው።


እስረኛውና ጠባቂዋ በስም ቢመሳሰሉም ዝምድና ግን የላቸውም። ባለሥልጣናት እንደሚሉት እስረኛው ኬሲ ዋይት የፖሊስ አባሏን መሳሪያ ይዞ ሊሆን ስለሚችል የታጠቀና አደገኛ ነው ተብሎ ይታሰባል።

የላውደርዴል ካውንቲ ፖሊስ አዛዥ ሪክ ሲንግልተን በሰጡት መግለጫ መርማሪ መኮንኗ ለባልደረቦቿ እስረኛውን ለአዕምሮ ጤና ግምገማ ፍርድ ቤት ልታደርሰው እንደሆነ በመንገር ከእስረኛው ጋር እስር ቤቱን ለቀው ወጥተዋል።

ከዚያም ጤንነት እየተሰማት ስላልሆነ ህክምና ለማግኘት እንደምትጥር መናገሯን የፖሊስ አዛዡ ተናግረዋል። ሁለት ሰዓታት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ግን መኪናዋን በአንድ የንግድ ማዕከል የመኪና ማቆሚያ ስፍራ ውስጥ ተገኝቷል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

ከዚያ በኋላም ባለሥልጣናት እስረኛው ወደ እስር ቤቱ አለመመለሱንና ማንም መኮንኗን ሊያገኛት እንዳልቻለ ተረዱ። ይህንንም ተከትሎ የአሜሪካ የማርሻል አገልግሎት ኬሲ ዋይትና ቪክ ዋይት ያሉበትን ለሚጠቁም እስከ 10 ሺህ ዶላር ድረስ እንደሚሸልም አስታውቋል።

የአሜሪካ ማርሻል ኬሲ ዋይት ለመኮንኗ እና ለሕዝቡ ደህንነት ስጋት እንደሆነ እንደሚታመን በመግለጫው አመልክቷል።



እስረኛው ኬሲ ዋይት (በግራ) እና የማረሚያ ቤት መኮንኗ ቪኪ ዋይት

ሼሪፍ ሲንግልተን እንዳሉት የእስር ቤቱ ተቆጣጣሪ መኮንኗ በሥራ ክፍሏ ለ25 ዓመታት አገልግላለች።

የእርምት ረዳት ዳይሬክተር ስትሆን እስረኞችን ወደ ፍርድ ቤት መውሰድ ከኃላፊነቶቿ መካከል አንዱ ነው።

እስረኛውን ወደ ፍርድ ቤት ለመውሰድ በራሷ የወሰነችው ውሳኔ ፖሊሲን የሚጥስ መሆኑን የተናገሩት የፖሊስ አዛዡ፤ “እንደዚህ በከባድ ወንጀል የተከሰሰ ሲንቀሳቀስ በሁለት ፖሊሶች መታጀብ አለበት” ብለዋል።

በመርማሪዋ መጥፋት እና በክስተቱ ሁሉም ሠራተኛ ተደናግጧል ብለዋል።

ሼሪፍ እንደሚሉት እርሷን ከመውቀሳቸው በፊት ጥፋተኛ መሆኗን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማየት እንደሚፈልጉም አክለዋል። “እንዲያመልጥ አግዛው ነው? ወይስ ይዛው ስትሄድ አግቷት ነው? የሚለውን እየመረመርን ነው” ብለዋል።

እስረኛው ዋይት የ38 ዓመት ጎልማሳ ነው። እአአ በ2020 በ58 ዓመቷ ኮኒ ሪጂዌይ በስለት በመግደል በሁለት ከባድ የግድያ ወንጀሎች እንደተከሰሰ የአሜሪካ ማርሻል አገልግሎት አስታውሷል።

የአሜሪካ የፌዴራል ሕግ አስከባሪ ኤጀንሲ በበኩሉ ግለሰቡ እአአ በ2015 ማጭበርበርን እና የተሽከርካሪ ስርቆት ጨምሮ በተከታታይ የወንጀል ድርጊቶች በቀረበበት ክስ በእስር ላይ እንደነበር አስታውቋል።

ግለሰቡ ግድያውን መፈፀሙን በማመኑም በሎዴርዴል ካውንቲ እስር ቤት ውስጥ የፍርድ ሒደቱን እየተጠባበቀ ሳለ መጥፋቱንም ባለሥልጣናት ገልጸዋል።



የተመድ ዋና ጸሐፊው አንቶኒዮ ጉቶሬዝ እና የሴኔጋል ፕሬዚዳንት ማኪ ሳል

## የተመድ ዋና ጸሐፊው አንቶኒዮ ጉቶሬዝ ቡርኪናፋሶ፣ ጊኒና ማሊ በፍጥነት ወደ ሲቪል አገዛዝ እንዲመለሱ አሳሰቡ

በጋዜጣው ሪፖርተር

ሶስቱም ሀገራት ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በመፈንቅለ መንግሥት ሲታመሱ የቆዩ ሀገራት ናቸው የጊኒው ጁንታ ባወጣው መግለጫ ‹‹ስልጣን ወደ ሲቪል አስተዳደር ለማሸጋገር ቢያነስ 39 ወራት ያስፈልገኛል›› ብሏል፡፡

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ኃላፊ አንቶኒዮ ጉቴሬዝ ቡርኪናፋሶ፣ ጊኒና ማሊ በፍጥነት ወደ ሲቪል አገዛዝ እንዲመለሱ አሳስበዋል። አገራቱ በሳህል ቀጠና ካለው የጂሃዲስት ዓመጽ ጋር በተያያዘ ከፍተኛ ትግል ሲያደርጉ የነበሩ ሀገራት ቢሆኑም ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ፤ በወታደራዊ መፈንቅለ መንግሥት ሲታመሱ የቆዩ ናቸው።

በአፍሪካ ‹‹የረመዳን የአጋርነት ጉብኝት›› ላይ የሚገኙት ጉቴሬዝ፤ ሴኔጋል ዳካር ከፕሬዚዳንት ማኪ ሳል ጋር በነበራቸው ቆይታ ሶስቱም ሀገራት በፍጥነት ወደ “ህገ-መንግሥታዊ ሥርዓት” ሊመለሱ ይገባል ማለታቸውን ኤ.ኤፍ.ፒ ዘግቧል።

በማሊ በነሐሴ 2020 እና በግንቦት 2021፤ በጊኒ መስከረም 2021 እንዲሁም በቡርኪናፋሶ በጥር 2022 መፈንቅለ መንግሥት እንደተካሄደ ይታወሳል። የሴኔጋሉ ፕሬዚዳንት ማኪ ሳል፤ ሶስቱንም ሀገራት ከአባልነት ያገደው የምዕራብ አፍሪካ ህብረት ኢኮዋስ ሊቀመንበር ናቸው።

የምእራብ አፍሪካው ተቋም ኢኮዋስ በማሊ በጥር ወር ከፍተኛ ማዕቀብ ቢጥልም፤ የማሊው ወታደራዊ ኃይሎች ስብስብ እስካሁን ስልጣን ወደ ሲቪል መመለስ ሳይችል ቀርቷል።

ኢኮዋስ ጊኒ እና ቡርኪናፋሶ ስልጣንን በፍጥነት ወደ ሲቪል አገዛዝ ማሸጋገር ካልቻሉ “በምክንያታዊ” የጊዜ ገደብ ውስጥ ተመሳሳይ ማዕቀብ ሊጣልባቸው እንደሚችል ማስጠንቀቁ አይዘነጋም።

ነገር ግን የሁለቱም ሀገራት ወታደራዊ መንግሥታት፤ ኢኮዋስ ያወጣውን የጊዜ ሰሌዳ አልተቀበሉትም። የቡርኪናፋሶው ወታደራዊ ኃይል ቀደም ብሎ ይፋ ያደረጉትን የሶስት ዓመት የሽግግር ጊዜ ለማሳጠር እቅድ እንደሌለው መግለጹ ይታወሳል፡፡

በተመሳሳይ ኢኮዋስ፤ የጊኒው ወታደራዊ ኃይል ቢያንስ በ16 ወራት ውስጥ ስልጣኑን ለሲቪል አስተዳደር ማስረከብ አለበት የሚል የጊዜ ገደብ አስቀምጦ የነበረ ቢሆንም፤ የጊኒው ጁንታ የኢኮዋስን ምክረ-ሃሳብ እንደማይተገብር በትናንትናው እለት ባወጣው መግለጫ አረጋግጧል።

# ስፖርት

## የአፍሪካ የዞን 4.4 የቼስ ቻምፒዮና በኢትዮጵያ እየተካሄደ ነው

**ቦጋለ አበበ**

ኢትዮጵያ የአፍሪካ የዞን 4.4 የግል የበላይነት የቼስ ቻምፒዮናን እያስተናገደች ትገኛለች። ቻምፒዮናው ካለፈው እሁድ ጀምሮ በአዲስ አበባ ከተማ ማግኖሊያ ሆቴልና ኮንፈረንስ ማእከል እየተካሄደ ሲሆን ለሰባት ተከታታይ ቀናት የሚቆይ ይሆናል።

ቻምፒዮናውን አስመልክቶ የኢትዮጵያ ቼስ ፌዴሬሽን ሰሞኑን በሰጠው መግለጫ፣ ኢትዮጵያ የ2022 የአፍሪካ "የዞን 4.4 የግል የበላይነት የቼስ ቻምፒዮናን " በስኬት ለማስተናገድ በቂ ዝግጅት ማድረጓን ገልጿል። "አንድ ቤተሰብ ነን( We are one family)" በሚል መሪ ቃል እየተካሄደ የሚገኘው ቻምፒዮና ከመጀመሪያው ቀን አንስቶ ጠንካራ ፉክክር እያስተናገደም ይገኛል

በዚህ የዞን 4.4 የግል የበላይነት የቼስ ቻምፒዮና ላይ ከአሥራ ሶስት የአፍሪካ አገራት የተውጣጡ የቼስ ተጫዋቾች እየተሳተፉ ይገኛሉ። የቻምፒዮናው ዋና አላማ ከአፍሪካ አገራት ጋር ያለንን የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ትስስር በማጎልበት ወዳጅነታችንን ከማጠናከር ባለፈ ኢትዮጵያን በማስተዋወቅ ለሌሎች የዓለም አገራት መልካም ገፅታዎችን ለማሳየት እንደሚጠቅም የኢትዮጵያ ቼስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ኢንጂነር ፀደቀ ይሁኔ ገልፀዋል ።

በቻምፒዮናው ኤርትራ፣ ሶማሊያ፣ ኬንያ፣ ጅቡቲና ሱዳን ተሳታፊ ከሆኑ አገራት መካከል የሚጠቀሱ ሲሆን፣ ይህ ውድድር በኢትዮጵያ መካሄዱ የቼስ ስፖርትን የበለጠ ለማስፋፋት የራሱ አዎንታዊ ሚና እንደሚኖረው ተጠቁሟል። በዚህ ውድድር እያንዳንዱ ሀገር አምስት ወንድና አምስት ሴት ስፖርተኞችን የሚያሳትፍ ይሆናል። ኢትዮጵያ አስተናጋጅ ሀገር እንደመሆኗ ሌሎች ከሚያሳትፉት በእጥፍ ስፖርተኞችን ታሳትፋለች። በተጨማሪም አሥር ኢትዮጵያውያን ስፖርተኞች በአፍሪካ ቼስ ኮንፌዴሬሽን በቀጥታ ተወክለው በግል ይወዳደራሉ።



በቻምፒዮናው ኢትዮጵያውያን ቼስ ተጫዋቾች ለአሸናፊነት ይጠበቃሉ፣

ኢትዮጵያ የ2022 ዓ.ም የዞን 4.4 የግል የበላይነት የቼስ ቻምፒዮና አዘጋጅ አገር በመሆኗ በውድድሩ ከሚፈቅደው ተሳታፊ ቁጥር በላይ ተጨማሪ ቡድን በአፍሪካ ቼስ ኮንፌዴሬሽን ቀጥታ ፈቃደኝነት መጨመር እንደተቻለ ታውቋል። በዚህም በአጠቃላይ ከመደበኛው ቡድን ውጪ ከዘጠኝ በላይ የግል ተወዳዳሪዎችን ማሳተፍ የተቻለበት ዕድል እንደተፈጠረ የኢትዮጵያ ቼስ ፌዴሬሽን የፅህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ሰይፈ በላይነህ በጋዜጣዊ መግለጫው ላይ ተናግረዋል።

በቻምፒዮናው ላይ ከአምስት ሺ አምስት መቶ የአሜሪካን ዶላር በላይ የማግኘት ዕድል ሰፊ መሆኑ የተጠቆመ ሲሆን ከሁለቱም ፆታ ቻምፒዮን ለሚሆኑ ሁለት ተጫዋቾች ሙሉ ወጪ ተሸፍኖ በአረብ ኢምሬት የ2022 ሻርጃህ ማስተር ቼስ ቻምፒዮና ላይም የመሳተፍ ዕድል ሊኖር እንደሚችል አቶ ሰይፈ ተናግረዋል።

በቻምፒዮናው የመወዳደሪያ ፔሪንግ ሲስተም ከአንድ አገር የተሰለፉ ተጫዋቾችን እርስ በርስ የሚገናኙበት እና የሚሸናነፉበት የውድድር አይነት እንደሚኖር የተጠቆመ ሲሆን፣ የአፍሪካ ቼስ ኮንፌዴሬሽን (ACC) እና የኢትዮጵያ ቼስ ፌዴሬሽን (ECF) በጋራ በመሆን ውድድሩን እንዳዘጋጁ ለማወቅ ተችሏል።

ከቻምፒዮናው ጎን ለጎን የተለያዩ መርሐግብሮች የተካተቱ ሲሆን ለአብነት ያህል የኢንተርናሽናል የዳኝነት ስልጠና ፣ በአዲስ አበባ የሚገኙ ሜጋ ፕሮጀክቶች እና የሙዚየም ጉብኝት ፣የባህል ትውውቅ እና የእራት ግብዣ እና የሽልማት እና የስጦታ መርሐግብሮች እንደሚኖሩ ተብራርቷል ።

በዚህ ቻምፒዮና ላይ በአጠቃላይ በሁለቱ ፆታ ከስልሳ በላይ የቼስ ተጫዋቾች ከተለያዩ አሥራ ሶስት የአፍሪካ አገራት ተሳታፊ ናቸው። በዚህም ከታዳጊ ወጣቶች ጀምሮ እስከ አዋቂዎች ድረስ ከስድስት የተለያዩ የኢትዮጵያ ከተሞች ሃያ የቼስ ተጫዋቾች ተመርጠው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ተወዳዳሪ ሆነዋል። ስፖርተኞቹ በውድድሩ ላይ ለመሳተፍ ቀደም ብለው በቂ ዝግጅት እንዳደረጉም ከፌዴሬሽኑ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

## በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት

ለኤን.ኤፍ.ኤ ቢዝነስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር /N-F-A Business PLC/ በከሳሽ የኢትዮጵያ ኤሌክትክ አገልግሎት አርባ ምንጭ ዲስትሪክት እና በተከሳሽ ለኤን.ኤፍ.ኤ ቢዝነስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር /N-F-A Business PLC/ መካከል ስላለው ክስ ጉዳይ ግንቦት 02/2014 ዓ.ም ቀጠሮ ከቀኑ 08፡00 ሰዓት በጋሞ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፌደራል ችሎት እንዲቀርቡ ተከሳሽ በጥሪው መሰረት የማይቀርቡ ከሆነ ጉዳዩ በሌሉበት የሚታይ መሆኑን የጋሞ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አዟል፡፡

**ጋሞ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት**

## አማራ ክልል

1.ሙሉቀን አለባቸው እና ጓደኞቻቸው የወተት ላም እርባታ 2. አቶ አለባቸው መኮንን ባንየው 3. አቶ ሽፈራው አባትሁን አሰጉ ባሉበት በከሣሽ አብቁተ የትኖራ ቅ/ጽ/ቤት በተከሣሽ 1. ሙሉቀን አለባቸው እና ጓደኞቻቸወ የወተት ላም እርባታ 2. አቶ አለባቸው መኮንን እንየው 3. አቶ ሽፈራው አባትሁን አሰጉ መካከል ስላለው የገንዘብ ክስ ክርክር ጉዳይ በከሳሽ ክስ ቀርቦብዎት ለግንቦት 09/2014 ዓ.ም. ስለተቀጠረ በቀጠሮው ቀን ምስ/ጎጃም/ዞን ከፍ/ፍ/ቤት ቢቸና ፕላዝማ ጽ/ቤት ችሎት እንዲቀርቡ የማይቀርቡ ከሆነ ግን በሌሉበት ታይቶ የሚወሰን መሆኑን እንዲያውቁት ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**በአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የምስ/ጐጃም/ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢቸና ከተማ ወ/ፍ/ቤት**

## ኦሮሚያ ክልል

በአመልካች ጌቱ ደፋሩ እና በተጠሪ አስቴር ተሰራ መካከል ስላለው የፍታብሄር ክርክር አስመልክቶ ይህ ፍርድ ቤት በቀን 19/08/2014 በዋለው ችሎት በሰጠው ትእዛዝ ለ3/9/2014 ዓ.ም በ3፡00 ሰዓት የአዳማ ወረዳ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት እንዲቀርቡ ሲል ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የአዳማ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት የፍታብሔር ችሎት**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም ኤፍ ኬ ኤክስፐሎረር ኢትዩጵያ ጉዞና አስጎብኚ/ኃላ/የተ/የግል ማህበር የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-59577 የተሽከርካሪው አይነት የመስክ ተሽከርካሪ የሻንሲ ቁጥር JN8CY15Y79×476362 ሞዴል TVTSLEFY61NKA-BB-H የሞተር ቁጥር TD42-210829 የሊብሬ ቁጥር 048557/617444/198604 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 19/8/2014 አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገኛ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቦሌ ቅ/ጽ/ቤት**

በከሳሽ አቶ ዮናስ ሙሉ አባትነህ እና በተከሳሽ አቶ ቦንዷ ፈይሳ ጣፋ መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ አቶ ቦንዷ ፈይሳ ጣፋ በተከሰሱበት ጉዳይ ለግንቦት 4 ቀን 2014 ዓ/ም 8፡00 ሰዓት ለሆነው ቀጠሮ እንዲቀርቡ ሲል የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ን/ስ/ላ ምድብ ችሎት አዟል፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የንፋስ ስልክ ላፍቶ ምድብ ችሎት**

የባለንብረት ስም ካርቱሪ አግሮ ፕሮዳክት ኃ/የተ/ የግልማህበር የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-70204 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ11 ኩንታል ያነሰ የሻንሲ ቁጥር MAT4450529ZL34686 ሞዴል 275 IDI የሞተር ቁጥር 275IDI05JQZSA0459 የሊብሬ ቁጥር 106358 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 20/8/2014 አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገኛ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቦሌ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ነቢሃ ኡመር አብደላ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-A30564 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር NZE120-3062457 ሞዴል CBA-NZE120-AEpNK የሞተር ቁጥር 2NZ-3274913 የሊብሬ ቁጥር 243330 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 7/8/2014 አመልክተዋል። የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገኛ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአቃቂ ቃሊት ቅ/ጽ/ቤት**

በከሣሽ አቶ መስፍን ሲሳይ እና በተከሣሽ ወ/ሮ አስቴር ጉታ ሰንበቱ መካከል ስላለው የፍቺ ክስ ጉዳይ ተከሣሽ ወ/ሮ አስቴር ጉታ ሰንበቱ በ1/9/2014 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቦሌ ምድብ 5ኛ ቤተሰብ ችሎት እንዲቀርብ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

የባለንብረት ስም የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጠን የሰሌዳ ቁጥር ኢት 04-01-28704 የተሽከርካሪው አይነት ድርብ አገልግሎት የሻንሲ ቁጥር MROFR22G160718526 ሞዴል KUN25L-PRMDHV የሞተር ቁጥር 2KD-5332037 የሊብሬ ቁጥር 0227311 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 13/8/2014 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገኛ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአቃቂ ቃሊት ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም አቶ ሰይፉ ወ/ኪዳን ወ/ሚካኤል የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-A18802 የተሽከርካሪው አይነት ድርብ አገልግሎት የሻንሲ ቁጥር JTFEG426510023177 ሞዴል RZN147L-PRMDSV የሞተር ቁጥር 1RZ-2478115 የሊብሬ ቁጥር 173914 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 21/8/2014 አመልክተዋል፡፡የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገኛ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቦሌ ቅ/ጽ/ቤት**

ከሳሽ/አመልካች ሲኖ ሃይድሮ ኮርፖሬሽን ኤልቲዲ ጌዶ ማና ቤኛ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት በተከሣሽ/ተጠሪ ሌልሳ ድርማቹ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ መካከል በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 1ኛ ችሎት ባለው ክርክር ጉዳይ ተከሳሾች/ተጠሪዎች መልስ እና ማስረጃቸውን በሬጅስትራር በኩል ለ128/8/2014 ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት እንዲቀርቡ እና ክስ ለመስማት ለ16/9/2014 ዓ.ም በ3፡30 ሰዓት በችሎት እንዲቀርቡ የልደታ ምድብ 1ኛ ኮንስትራክሽን ችሎት አዟል፡፡

**የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

የባለንብረት ስም ኤፍ.ኬ.ኤክስፐሎረር ኢትዮጵያ ጉዞና አስጎብኚ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-58497 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር SCP10-0237799 ሞዴል SCP10L-CHMGKW የሞተር ቁጥር 1SZ-0559978 የሊብሬ ቁጥር 027987 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 13/8/2014 አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገኛ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአቃቂ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት**